# ታህሳስ 23/2010

- አቃቤ ህግ አራት ምስክሮችን እንዳቀረበ በመግለፅ፤ ጭብጡን አስረዳ ሲባል ተከሳሾቹ በከሳቸው በቀረበው አግባብ መሰረት መሂኑን ተናግሮ ነበረ። በእለቱ ያልተሰየሙትን የችሎቱ መሃል ዳኛ ለሚሟላት የገቡት ዳኛ በሪሁ ዘሪሁን (ፕሬዝዳንት)፤ አቃቤ ህጉ ያቀረበው ጭብጥ ዝርዝር እና ገላጭ አለመሆኑን ተናግረው በእያንዳንዱ ተከሳሽ ምስክሩ የሚያስረዳውን ነገር (ጭብጥ) በአግባቡ እንዲያስመዘግብ አዘውታል።
- አቃቤ ህጉም (መኩሪያ አለሙ) "እኛ ባናምንበትም ፍርድቤቡ ካዘዘ .." በማለት ሲጀምር፤ ፕሬዝዳንቱ አቋርጠውት የታዘዘውን ብቻ እንዲያደርግ እና ትእዛዙን በተመለከተም አስተያየት ስጥ አለመባሉን በመግለፅ የታዘዘውን ብቻ እንዲፈፅም እና ሁለተኛ ተመሳሳይ ነገር እንዳይደግም አስጠንቅቀውታል።
- ምስክሩ በ2ኛ፣ 38ኛ፣ 33ኛ፣ 32ኛ እና 34ኛ ተከሳሾች ላይ በቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ነሐሴ 28/2008 ቀን በቃጠሎው ወቅት ተሳታፊ መሆናቸውን እና ከእለቱ አስቀድሞም ዝግጅት እንደነበረ የሚመሰክር መሆኑን አቃቤህግ በጭብጥነት አስመዝግቧል።

**በመጀመሪያ የቀረበው ምስክር የሰጠው ምስክርነት**

- ✓ አቶ በድሉ በላይ እንደሚባል... በቂሊንጦ ቃጠሎ ወቅት በዞን 2 የ5ኛ ቤት ከታሳሪዎች መሃል የተመረጠ አስተዳደር መሆኑን ተናግሯል።
- ✓ ምስክሩ የሚመሰክርባቸው ተከሳሾች፤ ወልዴ ሞቱማ፣ ቶፊክ ሽኩር፣ ሽምሱ ሰይድ፣ ከድር ታደለ እና ሲሳይ ባቱ እንደሚባሉ ጠቅሶ፤ ወልዴ ሞቱማን፣ ቶፊክ ሽኩርን እና ሽምሱ ሰይድን ብቻ በችሎት ለይቶ አሳይቷል።
- ✓ ዳኞች የተቀሩትን ሊመሰክርባቸው የመጣባቸውን ተከሳሾችች ለምን መለየት እንዳልቻለ ሲጠይቁት፤ ካሉት ተከሳሾች ውስጥ ስላላያቸው መሆኑን ተናግሮ ነበር። ነገር ግን አቃቤ ህግ በድጋሜ ሲጠይቀው መለየት ስላልቻለ መሆኑ ተናግሯል።
- ✓ ሽምሱ ሰይድ በ28/12/2008 ጠዋት ላይ ዩኒፎርሙን አውጥቶ "ይሄን ያላወለቀ ቡሽቲ ነው እናቱ ትበዳ" ብሎ ሁሉም ተከሳሾች እንዲያወልቁ ማድረጉን
- ✓ በግሩፕ የመደራጀት ነገር እንደነበር፤ ወልዴ ሞቱማ በሽብር ተከሶ እንደመጣ እና በተለያዩ አካባቢዎች ለሞቱ ሰዎች የህሊና ፀሎት እናደርጋለን እያለ እንደሚሰበስብ፤ በተጨማሪም አልጋ ላይ ይሰባሰቡና የኦነግን አላማ እንደሚደግፉ እና እንደሚቀላቀሉም እንደሚያወሩ
- ✓ ድምፃችን ይሰማ የሚባል ግሩፕ እንዳለ፤ ከሳቸው ምን እንደሆነ እንደማያውቅ ግን ሽብር እንደሚመስለው፤ ከድር ታደለ የቃጠሎው ቀን "ምግብ አንበላም ድምፃችን ይሰማ ቤተሰቦቻችን ይስሙልን" በማለት ጮክ ብሎ ሲናገር እንደነበር
- ✓ ከድር ታደለ የድምፃችን ይሰማ አባል መሆኑን ሲናገር ሰምቶት ያውቅ እንደሆነ ምስክሩ ተጠይቆ አባል ነኝ ብሎ ሲናገር ሰምቶት እንደማያውቅ ግን ሌላ ሰው አባል መሆኑን እንደነገረው
- ✓ ሲሳይ ባቱ የሚባለው ተለሳሽ እሳት ይዞ 5ኛ ቤት የሚገኝ የተደረደረ ፍራሽ ላይ እንደለኮሰው፤
- ✓ ሲሰይ ፍራሹ ላይ ሲለኩስ የት ሆኖ እንዳየው ሲጠየቅ፤ በአይኑ እንዳላየ ነገር ግን ሸዋሮቢት ምርመራ ሰአት ላይ ከሰጠው ቃል እንደተረዳ
- ✓ ቶፊክ ሽኩር እና ሽምሱ ሰይድ ነፃነት አበበ የሚባል እስረኛ ሲደበድቡ እንደነበር እና በኋላ ላይም ነፃመት ሞቷል የሚባል ወሬ መስማቱን
- ✓ ወልዴ ሞቱማ በቃጠሎው ቀን ሲሯሯጥ እንደነበር፤ "ፖሊሶች የሉም ወደውጪ እንውጣ" ሲል እንደነበር
- ✓ ተሰብስበው በግሩፕ የሚያወሩት ስለተከሰሱበት ጉዳይ ይሁን አይሁን እንደማያውቅ
- ✓ ብዙ ታራሚዎች ምግብ አንበላም ብለው ሲናገሩ እንደነበረ፤ የከድር ታደለ የሚለየው ጮክ ብሎ "ድምፃችን ይሰማ ቤተሰቦቻችን ይስሙልን" ስላለ መሆኑን
- ✓ ለቃጠሎው መንስኤ የሆነው የቤተሰብ ምግብ መከልከሉ መሆኑን
- ✓ በወቅቱ የእሳት ጭስ፣ ተኩስ እና የአድማ በታኝ ጭስ እንደነበረ እና እስረኞች ተዘግቶ የነበረውን የውጪ (የዞን) በር ሰብረው መውጣታቸውን

*መስክሮ ተመልሷል።*

- ሁለተኛው ምስክር ሰለሞን አስፋው እንደሚባል እና በ20ኛ ተከሳሽ አጥናፉ አበራ በ28/12/2008 ቀን የነበረውን ተሳትፎ እና ከዛ በፊትም ዝግጅት እንደነበረ የሚያስረዳ ምስክር መሆኑ በአቃቤ ህግ ተገልፆል።

*ሁለተኛው ምስክር የሰጠው ምስክርነት*

- ✓ ምስክሩ በወቅቱ ከአጥናፉ ጋር ዞን አንድ 6ኛ ቤት አብረው እንደነበሩ ገልፆል። አጥናፉንም ከችሎት ለይቶ አሳይቷል። በአሁኑ ሰአት ከእስር ተፈቶ በቦሌ ክፍለከተማ የሚገኝ ወረዳ ውስጥ ኮሚኒኬሽን ኦፊሰር በመሆን እየሰራ እንደሚገኝ ተናገሯል።
- ✓ አጥናፉ፤ ስለ ግንቦት 7 እንቅስቃሴ በቤት ውስጥ እና ግቢ ውስጥ ላሉ እስረኞች መግለጫ እንደሚሰጥ፤
- ✓ "ከጎንደር ይመጡ የነበሩ እህል የጫኑ መኪኖች ተቃጠሉ፤ ኢህአዴግ እሱ ወያኔ ነው የሚለው ፥ ወያኔ 3 ወር ቀራት እያለ" ታራሚው በኢህአዴግ ላይ ተስፋ እንዲቆርጥ የማድረግ ስራ ይሰራ እንደነበር እና ወሬዎችን ያሰራጭ እንደነበር
- ✓ ምስክሩ "በወቅቱ እርስዎ በኢህአዴግ ተስፋ ቆርጠው ነበር?" ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ፤ "አዎ" ሲል መልሷል
- ✓ አጥናፉ በቂሊንጦ ቆይታው አንድ ቀን ብቻ ቤተሰብ ተጠርቶ እንደነበር
- ✓ ግንቦት 7 በኢህአዴግ ላይ አብላጫ እንዲኖረው እና ከግቢ ውጪ ያለው ነገር ሰላማዊ እንዳልነበር ያወራ እንደነበር
- ✓ በቴሌቭዥን መግለጫ ሲሰጥ ጮክ ብሎ የማጥላላት ወሬ እንደሚናገር ፣ ባለስልጣናት ሲታዩ ውሸታም እንደሚል፤ ቻናል እስከማስቀየርም እንደሚደርስ
- ✓ በ26/12/2008 ማታ ላይ የቤተሰብ ምግብ የማይገባ ከሆነ የማረሚያ ቤቱንም አንበላም፤ አተት ያለበት የማረሚያ ቤቱ እንጂ የቤተሰብ ምግብ እንዳልሆነ ሲናገር እንደሰማው
- ✓ በ28/12/2008 ጠዋት ውጪ ላይ ተኩስ ከቅርበት ይሰማ እንደነበር፣ ይኖሩበት የነበረው ዞን ግቢ ውስጥ እሳትም ይቃጠል እንደነበር፣ አጥናፍ በወቅቱ ከአልጋ ላይ ብረት አንስቶ እያስፈራራ እስረኞች ከቤቱ እንዲወጡ ሲያስገድድ እንደነበረ፤ እሱን (ምስክሩን) ግን እንዳላስገደደው፣ በዛ ሰአት ከቤት መውጣት ማለት በጥይት መመታት ማለት እንደሆነ
- ✓ አጥናፍ እስረኞችን እንዲወጡ ሲያደርግ "ወንድሞቻችን እየሞቱ እየተገደሉ እኛ ቁጭ አንልም" ሲል እንደነበረ፤
- ✓ አጥናፍ "ወንድሞቻችን እየሞቱ .. " ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ምስክሩ ተጠይቆ ነበር። አንድ እስረኛ ከቤት ወጥቶ ግቢ ውስጥ እያለ እግሩን በጥይት ተመቶ ተመልሶ መምጣቱን በማየቱ እንደሆነ
- ✓ አጥናፍ ውጡ ብሎ ካስወጣቸው መሃል በጥይት የተመታ እስረኛ እንደሌለ
- ✓ ለቂሊንጦ ቃጠሎ ዋነኛው መንስኤ የምግብ መከልከሉ መሆኑን፤ በሁለተኝነት ግን በግቢ ውስጥ ይናፈሱ የነበሩ ወሬዎች እስረኛውን ተስፋ ያስቆርጡት ስለነበር መሆኑን

*መሰከሮ ተመልሷል።*

- አቃቤ ህግ አቅርቧቸው የነበሩት አራት ምስክሮች ነበሩ። ሆኖም ሁለቱ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት በቂው እንደሆነ በመናገሩ ቀሪዎቹ ሳይመሰክሩ እንዲመለሱ ተደርጓል።
- ቀሪ ምስክሮችን ለማቅረብ ፖሊስ የተያዘው ቀጠሮ ለትላንት ብቻ እንደተያዘ በማሰብ ምላሽ ማቅረቡን አቃቤህግ የተናገረ ሲሆን ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ያሉ 4ት ምስክሮቹን እንዲቀርቡለት መጥሪያ እንዲወጣለት ጠይቋል።

- ተከሳሾች ለ5ወር የተሰጣቸው ቀጠሮ አቃቤ ህግ ምስክሮቹን ፈላልጎ እንዲያቀርብ በቂ ጊዜ እንዲኖረው ተብሎ መደረጉን ገልፀው፤ ከ5 ወር በኋላ ቆይተው ሲመጡ ፖሊስ ለ2ት ሳምንት የተያዘውን ቀጠሮ አላውቀም ማለቱ አሳማኝ እንዳልሆነ፤ እንዲሁም ከማረሚያ ቤት አቀርባቸዋለው ያላቸውን ምስክሮች አቃቤህግ ያስጠናቸው ምስክሮች እንጂ በባለፈው ቀጠሮ ከማረሚያ ቤት የሚቀርቡ ምስክሮችን መጨረሱን ገልፆ እንደነበር በብስጭት ተናግረዋል።

- በእለቱ ያልተሰየሙትን የመሃል ዳኛ ለሚሟላት የገቡት ዳኛ በሪሁ ዘሪሁን (ፕሬዝዳንት)፤ አቃቤ ህግ ከፖሊስ ጋር በመሆን በቅርበት በመስራት ምስክሮቹን እንዲቀርቡ ማድረግ የሱ ግዴታ መሆኑን በመግለፅ፤ ፖሊስ የተያዘውን ቀጠሮ አላወቀም የሚለው ምላሽ ተቀባይነት እንደማይኖረው በመግለፅ ቀሪ የአቃቤ ህግ ምስክሮችን ለመስማት በተያዘው ቀጠሮ መሰረት በአዳሪ ለነገ ታህሳስ 24/2010 ተቀጥሯል።

# ታህሳስ 24/2010

በዛሬው እለት ያቀረባቸው ምስክር ኦፊሰር ገ/ማርያም ወልዳይ እንደሚባሉ እና በመቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፣ በፍቅረማርያም አስማማው፣ በአበበ ኡርጌሳ፣ በአግባው ሰጠኝ፣ በአንጋው ተገኝ እና ዶ/ር ፍቅሩ ማሩ ላይ እንደሚመሰክሩ አቃቤ ህጉ ተናግሯል፡፡ ዶ/ር ፍቅሩ በ28/12/2008 ለደረሰው አደጋ ጉዳት ላደረሱ እስረኞች ብር ይሰጡ እንደነበር እና የተቀሩት ከላይ በስም የተጠቀሱት ተከሳሾች ደግሞ ቃጠሎው ከመድረሱ በፊት ከእስር ቤት ለማምለጥ ዝግጅት ሲያደርጉ እንደነበር ተደርሶባቸውም ተለይተው እንዲቀመጡ መደረጉን የሚያስረዱ መሆኑን አቃቤ ህግ አስረድቷል፡፡

- ምስክሩ የሚመሰክሩባቸውን እስረኞች በስም ከጠቀሱ በኃላ የምስክርነት ቃላቸውን መስጠት ከመጀመራቸው በፊት፡ 1ኛ ተከሳሽ መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ “በዘር ማጥፋት ሊጠየቅ የሚገባው ሰው ነው፡ እስረኛን በጥይት ገድሎ በእሳት ያቃጣለ ሰው ነው፡፡ ጅምላ መቃብር በእስር ቤት ውስጥ ያሰራ ነው፡፡” ሲል እንዲመሰክር አንፈልግም የሚል አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡ ሌሎች ተከሳሾችም “በህግ አምላክ ይውጣ!” ፤ “የድሃ ልጅ ገድሎ ማእረግ ተጨምሮለት ነው ለምስክርነት የቀረበው” ፤ “ሰው በጥይት ገድሎ በእሳት ያቃጠለ ነው” ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ ዶ/ር ፍቅሩ ተነስተው ለሌሎቹ ተከሳሾችን ተረጋግተው እንዲነጋገሩ ካግባቡ በኃላ ሁሉም ተከሳሾች ምስክሩ ምስክርነቱን እንዲቀጥል መስማማት ላይ ከደረሱ በኃላ ኦፊሰር ገ/ማርያም ወልዳይ ምስክርነታቸውን ቀጥለዋል፡፡

- ***ምስክሩ ኦፊሰር ገ/ማርያም ወልዳይ ከአቃቤ ህግ በቀረበላቸው ዋና ጥያቄ መሰረት የሰጡት ምስክርነት***

- ❖ መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ በሽብር የተከሰሱ ሰዎችን እያስተባበረ ከእስር ቤት ለማምለጥ ዝግጅት እያደረገ እንደነበር እና ተደርሶባቸውም አስተባባሪ ናቸው ያሏቸውን ግለሰቦች የመለየት ስራ በመስራት እቅዱን ማክሸፋቸውን፣ ስለእቅዱ እና ተያያዥ ጉዳዮች መረጃ የሚሰጧቸው ከእስረኞች የተመረጡ የቤት አስተዳደሮች መሆናቸውን
- ❖ ጌታቸር የተባለው ተከሳሽ ክሱ ሽብር ባይሆንም በሽብር ክስ የሚገቡ ሰዎችን እና ቦዘኔዎችን እያስተባበረ ብር እንደሚያቀባብል፡፡ እንዲሁም ከዶ/ር ፍቅሩ ገንዘብ እንዲያገኙ እና ችግር እንዲፈጥሩ እንደሚያደርግ፡፡
  [ምስክሩ ቦዘኔ የሚለውን ቃል መጠቀማቸውን በመቃወም ጌታቸር “እኛ የተከበረ ስራ የነበረን ሰዎች ነን፡፡ ምስክሩ ስብእናችንን በችሎት ፊት እየተጋፉ ነው ያሉት፡፡ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ይስጥልን” በማለት አስተያየቱን ሰጥቶ ነበር ዳኞችም ምስክሩን መክረው እንዲያስተካክሉ ነግረዋቸዋል፡፡]
- ዶ/ር ፍቅሩ ብር እያስመጡ ድጋፍ ያደርጉ እንደነበር፣ ብሩ እንዲገባ ፋሲል የተባለ አባላቸው ዶ/ር ፍቅሩን ተባብሮ መጠኑን የማያውቁት ገንዘብ እንዳስገባላቸው፣ ይህ ገንዘብም በቃጠሎው ወቅት ለተፈጠረው ህይወት መጥፋት እና ንብረት መውደም መነሻ መሆኑን
- ከቃጠሎው በኃላ የእስረኞች ሻንጣ ሲፈተሽ ብዙ ብር መገኘቱን፣ ሻንጣው ግን የማን እንደሆነ እንደማያውቁ

➢ በቃጠሎው የሞቱት 23 እስረኞች መሆናቸውን፣ አብዛኛዎቹ ህይወታቸው ያለፈው ዞን ሁለት ያሉ እስረኞች መተዋቸው 5ኛ እና 7ኛ ቤት አስገብተዋቸው በእሳት እንዳቃጠሏቸው፣ ሁለት እስረኞች ብቻ በአጥር ሊወጡ ሲሉ በጥይት ተመተው እንደሞቱ

➢ **ምስክሩ ኦፊሰር ገ/ማርያም ወልዳይ ከጠበቆች በቀረበላቸው ዋና ጥያቄ መሰረት የሰጡት ምስክርነት**

❖ በ28/12/2008 [የቃጠሎው ቀን] ከ ጠዋቱ 1፡30 ጀምሮ በቂሊንጦ በስራ ቦታቸው ገብተው ቀኑን ሙሉ እዛው እንደነበሩ፣ ጠዋት ላይ ድንጋይ የመወራወር እና የመጯጯህ ነገር እንደነበር

❖ ፋሲል ገንዘቡን ያስገባው መቼ እንደሆነ እንደማያስታውሱ፣ አባላት ሲገቡ ጥብቅ ፍተሻ እንደሚደረግ፣ የያዙት ምሳቃም ሆነ ማንኛውም ነገር ተፈትሾ እንደሚገቡ፣ ምሳቸውን በየቢሯቸው እንደሚመገቡ፣ እስረኞች ወዳሉበት ዞን ሲገቡ የምሳቃቸውን ይዘው መግባት እንደማይችሉ፣ ፋሲል ብር እንደሚያስገባ ከቃጠሎው በፊትም መረጃው ደርሷቸው የነበረ ቢሆንም በክትትል ቢደረግበትም ሊደረስበት አለመቻሉን

❖ ከቃጠሎው ከተወሰኑ ወራት በፊት አበበ ኡርጌሳ፣ ፍቅረማርያም አስማማው እና መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ ለብቻቸው ተለይተው ዞን 4 የሚባል ቦታ እንዲቀመጡ ከሌሎች እስረኞች እንዳይገናኙ መደረጉን፣ ነገር ግን ሆስፒታል እና ፍርድ ቤት ሲሄዱ ከሌሎች እስረኞች ጋር እንደሚገናኙ፣ በቃጠሎው እለትም እዛው እንደነበሩ፣ ዞን 4 እንዳልተቃጠለ፣ በውስጡ የነበሩ እስረኞችም ከክፍላቸው እንዳልወጡ

❖ በቂሊንጦ የሚገኝ እስረኛ ቤተሰቡ ሊጠይቀው ሲመጣ እየተመዘገበ በወር 200 ብር ድረስ ብቻ መቀበል እንደሚችል፣ ብሩ ከዛ በላይ ከሆነ ደግሞ ቢሮ ተቀምጦለት በሪሲት እየተቆረጠ እንዲወስድ እንደሚደረግ

❖ የማረሚያ ቤቱ አባላት ችግር እንደነበረባቸው እና የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር መኖሩን ግምገማ አድርገው እንደደረሱበት

❖ "የማረሚያ ቤቱ የጥበቃ እና ደህንነት ሁኔታ ከፍተኛ ነው ወይስ የላላ?" ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ መካከለኛ እንደሆነ፣ መካከለኛ ያሉበት ምክንያትም አባላት በገንዘብ እየተገዙ ህገወጥ ገንዘብ ያስገቡ ስለነበር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

❖ ከቂሊንጦ በፊት ሸዋሮቢት ማረሚያ ቤት እንደነበሩ፤ ሸዋሮቢት የጥበቃ ሁኔታው ከፍተኛ እንደነበረ፣

❖ ታራሚዎች ሲወጡም ሲገቡም እንደሚፈተሹ፣ የሚኖሩበት ክፍልም በየሳምንቱ በየወሩ እንዲሁም ድንገተኛ ፍተሻ እንደሚደረግ፣ ነገር ግን የዶ/ር ፍቅሩ ቦታ ለፈታሾች ብር እየሰጡ አይፈተሽም የሚባል ወሬ ይሰሙ እንደነበር፣ ዶ/ር ፍቅሩ በቆዩበት 3ት አመት በፍተሻ ብር ተገኝቶባቸው እንደማያውቅ፣

❖ "ለኔ የተመደቡልኝ ፈታሾች ለብቻ ናቸው ወይስ 3ት አመት ሙሉ በፍተሻ ለሚመጡ አባላት ብር እየሰጠሁ ነው ፍተሻ እንዲያልፉኝ የማደርገው?" በማለት ዶ/ር ፍቅሩ ላቀረቡት ጥያቄ፤ ፍተሻውን የሚያደርጉት የተለያዩ አባላት መሆናቸውን እና ለዶ/ር የተመደቡ ፈታሾች አለመኖራቸውን ገልፀው "አልፎ አልፎ ፈታሾች ያልፏቸዋል" የሚባል ወሬ ይሰሙ እንደነበር ተናግረዋል

❖ ዶ/ር ፍቅሩ ጋር ሲደርሱ የማይፈትሿቸው አባላት እርምጃ እንዳልተወሰደባቸው

❖ በማረሚያ ቤቱ አሰራር አንድ እስረኛ ሊያመልጥ ሲል ከተደረሰበት በየደረጃው በጥይት እንደሚመታ፣ "በመጀመሪያ እግሩን እያለ እያለም ... ያስቀረዋል [መግደል]"

❖ በቃጠሎው ወቅት ሁለት እስረኞች በጥይት ተመተው መሞታቸውን ተናግረዋል፡፡ "ማነው ትእዛዝ ሰጠው?" ተብለው ተጠይቀው፡ "ተቋሙ ነው፡ አመራሩ" ሲሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በተቋሙ ትእዛዙን የሰጠውን ሰው ስም እንዲናገሩ በድጋሚ ተጠይቀው "በእለቱ ማንም ትእዛዝ አልሰጠም፡ በየዞኑ በሃላፊነት ያሉ ሁሉም ተኩሰዋል፡፡ ብዙ ጥይቶች ተተኩሰዋል፡፡"

❖ ጠበቃ ወንድሙ የሚኒስተሮች ምክር ቤት ለማረሚያ ቤት የታራሚዎችን አያያዝ በተመለከተ ያወጣው አዋጅ ላይ ሊያመልጥ የነበረን ወይም ያመለጠን እስረኛ እግርን መምታት ቀጥሎም ማስቀረት የሚል የቅጣት አይነት እንደሌለ ጠቅሰው፡ የሚመሩት በየትኛው ደንብ መሆኑን ለምስክሩ ጥያቄ አቅርበውላቸው ነበር፡፡ ምስክሩም ጠበቃው በጠቀሱት ደንብ እንደሚመሩ ገልፀውላቸዋል፡፡

- ምስክሩ 1ኛ ተከሳሽ መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ ላቀረበላቸው መስቀለኛ ጥያቄ ምስክሩ የሰጡት መልስ

መቶ አለቃ ማስረሻ፡ የማረሚያ ቤቱ የደህንነት ሃላፊዎች፤ ኤርሚያስ፣ ካህሱ፣ ጉዕሽ፣ ተሾመ እና እርስዎ ራስዎ እንዲሁም የዞን 1 ሃላፊ ዘሩ፣ የዞን 2 ሃይለ እና የዞን 3 ሊላይ ሁላችሁም የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናችሁ አይደል?

ምስክር፡ አዎ

[ምስክሩ መልስ ከሰጡበት በኃላ አቃቤ ህግ ጥያቄውን ተቃውሞ አስተያየት ሰጥቶ ነበር፡፡ ምስክሩ የሚመሰክሩበት ጭብጥ ከትግርኛ ተናጋሪዎች ጋር ግንኙነት የለውም በሚል፡፡ መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤም ከዚህ ቀደም ምስክሮች ሲመሰክሩም ሆነ በክሱ ላይ የትግራይ ብሄሮችን ለማጥቃት የሚል ነገር አለው ብሎ ጥያቄው እንዲፈቀድለት ጠይቋል፡፡ ሆኖም "የትግራይ ተወላጆችን ለማጥቃት" የሚለው ሃረግ በክሱ ውስጥ ስለሌለ ጥያቄውን እንዲታለፍ ሲሉ ዳኞች ውሳኔ አስተላልፈዋል፡፡]

መቶ አለቃ ማስረሻ ፡ በ28/12/2008 በቃጠሎ ወቅት ጥይት ሲተኮስ ነበር ብለዋል፡፡ እርሶ አይደሉም ትእዛዙን የሰጡት?

ምስክር፡ አይደለሁም፡፡ ሁሉም ሃላፊ የራሱን እርምጃ ወስዷል፡፡ እኔ ትእዛዝ አልሰጠሁም፡፡

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ በህይወት ያሉ በጥይት የተመቱ አሉ?

ምስክር፡ ይኖራሉ አላውቃቸውም

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ ከዞን 2 ወደ ጨለማ ቤት መቼ መጣሁ?

ምስክር፡ ጨለማ ቤት የለንም፡፡ ወደ ማግለያ ቤት ነው የሄድከው

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ እሺ እናንተ ማግለያ ወደምትሉት እኛ ጨለማ ነው የምንለው መቼ መጣሁ?

ምስክር፡ ቀኑና ወሩን አላስታውሰውም ከቃጠሎው ሁለት ወር በፊት ይሆናል

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ ከዛም ፍርድ ቤት ስሄድ በፒካፕ ለብቻዬ ያመላልሱኝ ነበር?

ምስክር፡ አዎ አንድ ቀን

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ በሌላ ቀንም ከአባሪዎቼ ጋር እንዳልገናኝ በደህንነት ታጅቤ ወደፍርድ ቤት እንድመጣ ያደርጉ ነበር?

ምስክር፡ አዎ

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ በቃጠሎው እለት እኛ የነበርንበት ዞን በር እንዲከፈት እና ማስረሻ ሰጤ፣ በቀለ ገርባ እና ሌሎች በጥይት ይመቱ ብለው ትእዛዝ ሰጥተዋል አልሰጡም?

ምስክር፡ አልሰጠሁም

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ እሺ በሩ ይከፈትላቸው ብለው ትእዛዝ አስተላልፈዋል?

ምስክር፡ አዎ አስተላልፌአለው፡፡ ውጡ ሲባሉ አንወጣም ብለዋል ብለው ነግረውኛል

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ እኛ የነበርንበት ዞን 4 እሳት ካልተቀጣጠለ እና ምንም ችግር ካልነበረ ለምን እንድንወጣ ፈለጉ? ለምን በሩ ይከፈትላቸው አሉ?

ምስክር፡ መውጣት ምትፈልጉ ከሆነ ብዬ ነው፡፡ አንወጣም ስላላችሁ እዛው ቀርታችኃል

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ ከእስር ቤት የማምለጥ እቅዱ የኔ ከሆነ እንዴት ሳልወጣ ቀረሁ? እንዴት በሩ ሲከፈትልኝ አልወጣም አልኩ?

ምስክር፡ እሱን እርስዎ ነው የሚያውቁት

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ ዞን 3 የተቃጠለው እስረኛ ከወጣ በኃላ ነው አይደል?

ምስክር፡ አዎ

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ ዞን 2 በጥይት የተመቱትን ወንድሞቻችንን ዞን 3 ወስዳችሁ ያቃጠሏቿቸው እናንተ አይደላችሁም?

ምስክር፡ አይደለንም

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ እሺ በቃጠሎ ማግስት በ29፣ በ30 እንዲሁም ጳጉሜ 1፣ 2 እና 3 አስከሬን ተገኝቷል አይደል?

ምስክር፡ አልተገኘም፡፡ በ28 ነው ተሰብስቦ ያለቀው

መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ፡ በተፈጠረው አደጋ ተጠያቂ አይደለሁም ብለው ያምናሉ?

ምስክር፡ አይደለሁም

***የከሰዓቱ ችሎት ሰዐት ስላለቀ ምስክሩ ለሚቀርብላቸው ቀሪ መስቀለኛ ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጡ በአዳሪ እንዲቀርቡ ተነግሯቸዋል፡፡***

[1ኛ ተከሳሽ መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ በትላንትናው እለት የማረሚያ ቤት ሃላፊዎች የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ የሚያነሳው ጥያቄ ፍርድ ቤቱ እንዲፈቅድለት እና በክሱ ላይም "ትግሬዎችን መግደል ለፖለቲካው ጥሩ ስለሆነ .." የሚል ያለበትን ገጽ ጠቁሞ አሳይቷል፡፡ ዳኞችም በትላንትናው እለት ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ መሆኑን ጠቅሶ ገፁን ጠቅሶ ያነበበው ሃረግ የሚገኘው በሌላ ተከሳሽ ላይ በመሆኑ እሱን እንደማይመለከተው ገልጸውለት ሌላ ጥያቄ ካለው እንዲቀጥል ነግረውታል፡፡ መቶ አለቃ ማስረሻም "ለትግራይ ህዝብ የህውሃት አባላት ጠላት ይሆኑባቸዋል እንጂ እኛ የትግራይ ህዝብን የመግደል አላማ የለንም፡፡ ለትግራይ ህዝብ ጥላቻ እንዳለን ለማስመስከር እየተጣረ ነው፡፡ ህውሃት የራሱን የበላይነት ለማስቀጠል እነሱን እንደሚጠቀም እና ታራሚዎች በትግራይ ተወላጆች ላይ ጥላቻ አላቸው የሚለውን ለማሳየት ሲሰሩ ነበረ፡፡ ይሄን እንዲያስረዱልኝ ነው፡፡" ካለ በኃላም ጥያቄው ከጭብጡ ጋር አይገናኝም ስለተባለ "ፍርድ ቤቱ ጫና እያደረገብኝ ነው፡፡ ሌላ ጥያቄ መቀጠል አልፈልግም" በማለት ጥያቄ ማቅረቡን ትቶታል፡፡]

- **3ኛ ተከሳሽ ጌታቸር ለምስክሩ ኦፊሰር ገ/ማርያም ወልዳይ ያቀረበው ጥያቄ እና ምስክሩ የሰጡት ምላሽ**

ጌታቸር ጥያቄውን ከመጀመሩ በፊት ምስክሩ የማረሚያ ቤት ከፍተኛ ኃላፊ ከመሆናቸው አንፃር በሚያቀርብላቸው ጥያቄ ምክንያት ሊደርስበት ከሚችል አደጋ ፍርድ ቤቱ ዋስትና እንዲሰጠው ጠይቋል፡፡ በሌላ ክስ (ቀድሞ በተከሰሰበት መዝገብ) መስቀለኛ ጥያቄ በምናቀርብበት ጊዜ ማረሚያ ቤቱ ይጠብቀናል፡፡ "አሁን ግን እኝህ ሰውዬ ሃላፊ ስለሆኑ ጥያቄ ስላቀረብኩ ችግር ይፈጥሩብኛል ብዬ እሰጋለሁ" ብሏል ጌታቸር፡፡ ዳኞችም ችግር የለውም በማለት ጥያቄውን እንዲቀጥል ነግረውታል፡፡

ጌታቸር፡ ለበዓል በታራሚዎች ብር ይሰበሰባል አይሰበሰብም?

ምስክር፡ አይሰበሰብም

ጌታቸር፡ የታራሚዎች ኮሚቴ አሉ የሉም?

ምስክር፡ አሉ

ጌታቸር፡ እኔ የክልል አስተዳደር እንደሆንኩ ያውቃሉ? ምንድነው ስራዬ?

ምስክር፡ አዎ ለእስረኞች አስተባባሪ ነበርክ፡፡ መጨረሻ ላይ ግን ችግር እንዳለብህ መረጃ ደርሶን ከቤት አስተዳደር እንድትነሳ አድርገናል፡፡ ጊዜውን አላስታውሰውም ግን ቃጠሎው ከመድረሱ ከሶስት ሳምንት በፊት ይሆናል፡፡

ጌታቸር፡ የሽብር ተከሳሾች ለጥበቃ አስጊ ናቸው ብላችሁ ለኛ ለግቢ አስተዳደሮች ነግራችሁን ጥብቅ ፍተሻ ይደረግባቸው ነበር አልነበረም?

ምስክር፡ አዎ ጥብቅ ፍተሻ ይደረግ ነበር

ጌታቸር፡ በሽብር የተከሰሱ ግለሰቦች በግቢው ያሉ ሱቆች እንዳይሰሩ፣ በተለያዩ የስራ መደቦች እንዳይቀጠሩ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ተጠቃሚ አይደሉም አይደል?

ምስክር፡ እንደሱ አይነት ስራ የለም፡፡ ስራ የሚመደበው በሰውዬው ባሃሪ ነው፡፡ እርስዎም ይሰሩ አልነበር?

ጌታቸር፡ እኔ ክሴ ምንድነው?

ምስክር፡ አላስታውሰውም

ጌታቸር፡ ታዲያ ለምን ይፈርጁኛል? አይፈርጁአ!

ጌታቸር፡  በ26/12/2008 እርስዎ እና የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ባለበት የየቤቱን አስተዳደር ሰብስባችሁ የኮሌራ በሽታ ስለገባ የቤተሰብ ምግብ እንደማይገባ ለሌሎች ታራሚዎች እንዲነግሩ አልነገራችኃቸውም?

ምስክር፡ እኔ አልነበርኩም በስብሰባው ላይ

ጌታቸር፡ ምግብ ከቤተሰብ እንደማይገባ ማስታወቂያ ተለጥፏል አይደል?

ምስክር፡ አዎ

ጌታቸር፡ መቼ ነው የተለጠፈው

ምስክር፡ በ26/4/2008

ጌታቸር፡ የታራሚው ምላሽ ምንድን ነበር?

ምስክር፡ የቤተሰብ ምግብ ይግባልን ይሉ ነበር

ጌታቸር፡  በ28/12/2008 ረብሻው የተነሳው በምግብ ጥያቄ ነው?

ምስክር፡ አዎ

ጌታቸር፡ የቤተሰብ ምግብ እንደሚገባላቸው ቢነገራቸው ረብሻ ይነሳ ነበር?

ምስክር፡ አዎ፡፡ ምክንያቱም የማምለጥ ጥንስሱ ስለነበር፡፡

ጌታቸር፡ የማረሚያ ቤት አባል በፈለገ ሰዓት መተኮስ ይችላል?

ምስክር፡ አይችልም ነገር ግን ችግር በደረሰ ሰዓት ይተኩሳል፡፡

ጌታቸር፡ በእለቱ ምን ያህል ጥይት እንደተተኮሰ ያውቃሉ?

ምስክር፡ ባቅም ለእርስዎ አይመለከትም

[ፍርድ ቤቱ ጣልቃ በመግባት ምስክሩ ጥይት ሲተኮስ ነበር ማለታቸውን አስታውሰው የሚያውቁ ከሆነ እንዲመልሱ ነግረዋቸዋል]

ምስክር፡ አላውቅም

ጌታቸር፡ ዞን ሁለት 5ኛ እና 7ኛ ቤት እስረኞች ውስጥ ሆነው እንደተቃጠሉ ተናግረዋል፡፡ የት ሆነው ነው ያዩት?

ምስክር፡መረጃ ደርሶኝ ነው

ጌታቸር፡ ማነው መረጃውን የጠቆሞት?

ምስክር፡ ረስቼዋለው

ጌታቸር፡ እስረኞቹ የሞቱት በቃጠሎ ከሆነ ማን ለመሆናቸው ለይታችሁ ስም ሰጣችኃቸ?

ምስክር፡ እኔ አስከሬን አላየሁም

ጌታቸር፡ እርስዎ የጥበቃ እና የደህንነት ክፍል ሃላፊ ኖት እንዴት ይሄን ጉዳይ ሳይከታተሉ?

ምስክር፡ ውጪ የምሰራው ስራ ነበር

ጌታቸር፡ ዞን 2 ስንት ሰው ሞተ?

ምስክር፡ ቁጥሩን አላስታውስም

ጌታቸር፡ ዞን 1 ሰው ሞቷል?

ምስክር፡ አልሞተም

ጌታቸር፡ ዞን 3ስ?

ምስክር፡ አልሰማሁም

ጌታቸር፡ ወ/ሚካኤል ሃለፎምን እና ታደለ ብርሃኑን ያስታውሷቸዋል?

ምስክር፡ አዎ

ጌታቸር፡ ጋዲሳ ከኦሮሚያ የመጣ፣ አብዲሳ ነጋ እሱም ከኦሮሚያ ፣ ሰጠኝ ሙሉ አማራ የጎንደር ልጅ፣ መድሃኒት እስከዛው ከአማራ የመጣ፣ አባይነህ አሰፋ አማራ፣ ወጋየሁ ረጋሳ ኦሮሞ እና ያኬት ሪካ ከጋምቤላ ያስታውሷቸዋል?

ምስክር፡ አላስታውሳቸውም

ጌታቸር፡ የጠቀስኳቸው እስረኞች በቃጠሎው ወቅት የተገደሉ ናቸው፡፡የዞን ተጠሪ የነበሩ እና የናንተን ስራ የሚሰሩ ናቸው፡፡ ወ/ሚካኤል እና ታደለ ምንም ስራ የሌላቸው ከናንተ ጋር የሚያገናኛቸው ነገር የለም፡፡ እነዚህ ሰዎች ትግሬ ስለሆኑ ነው የለዩአቸው? ከናንተ ጋር የሚገናኙትን የሚሰሩትን ግን አላውቃቸውም አሉ፡፡

ጌታቸር፡ በእለቱ በመስጊድ በኩል በር ገንጥለው እዛ ገብተው ተደብቀው ነበር አልነበረም?

ምስክር፡ አልነበርኩም

ጌታቸር፡ ሜዳ ላይ አንድ ረዘም ቀላ ያለ አባል ይተኩስ ነበር አልነበረም?

ምስክር፡ አላየሁም

ጌታቸር፡ እርስዎች ሽጉጥ ይዘው ነበር?

ምስክር፡ ይዤ ነበር ግን አልተኮስኩም

ጌታቸር፡ እኛ ያለንበት ዞን መጥተው ወ/ሚካኤል ሃለፎምን በአንድ እጅዎ ታደለ ብርሃኑን አስከትለው በሌላኛ እጅዎ ሽጉጥ ይዘው አላወጧቸውም?

ምስክር፡ አላወጣኃቸውም

ጌታቸር፡ ሁለቱ በጥይት ተገደሉ ያሏቸው እስረኞች ምናቸውን ነው የተመቱት?

ምስክር፡ አላወቅኩም

ጌታቸር፡ ገመቹ የሚባል የማረሚያ ቤት ፖሊስ ስራ አቁሟል አይደል?

ምስክር፡ ከሚጠየቁት ውስጥ አንዱ ነው

ጌታቸው፡ ላስታውሶት ቃጠሎው በተነሳ ወቅት ወ/ሚካኤልን እና ታደለን ይዘው ሲወጡ ገመቹ "ለምንድነው ዘር እየመረጡ  የሚያወጡት እኔም ዘር እየቆጠርኩ ላውጣ ወይ?" አላሎትም?

ምስክር፡ አላለኝም

ጌታቸር፡ የሰው ህይወት እና ንብረት የጠፋው ገንዘብ በህገወጥ መንገድ በአባሎች ስለሚገባ ነው ብለዋል፡፡ መቼ ነው ገንዘብ የገባው?

ምስክር፡ አላስታውስም

ጌታቸር፡ ፋሲል መቼ ነበር ብር እንደሚያስገባ ያወቃችሁት?

ምስክር፡ ከቃጠሎ በኃላ

ጌታቸር፡ ችግሩ የተፈጠረው አባላችሁ የሆነው ፋሲል በሚያስገባው ብር ከሆነ ስለዚህ ችግሩ የተፈጠረው ጥብቅ ቁጥጥር ባለመኖሩ በእርስዎ እንዝላልነት ነው ማለት አይቻልም? መረጃው ከደረሳችሁ መያዝ ያልቻላችሁት? ድክመንቱ የማን ነው?

ምስክር፡ ብር የሚያስገቡ አባላት አና የናንተ

ጌታቸር፡ አባላችሁ በሆነው ፋሲል ብር እንደሚገባ መረጃው ደርሶናል ተከታትለን ግን ልንይዘው አልቻልንም ብለዋል፡፡ ተከታትላችሁ መያዝ የናንተ ድክመት አይደለም?

ምስክር፡ አይደለም

ጌታቸር፡ እሺ እርስዎ ምንም ስህተት አልሰራሁም ነው የሚሉት?

ምስክር፡ አዎ

ጌታቸር፡ ነሃሴ 28/2008 ከቃጠሎው በኃላ ማታ ከምሽት 4 ሰዓት ላይ ሸርጥ አንገቶት ላይ ጠምጥመው አጅበውን ሄደዋል አልሄዱም?

ምስክር፡ ሄጃለው

ጌታቸር፡ ሁሉም ታራሚ ሻንጣውን ይዘው ወጥቷል?

ምስክር፡ የተሰበሰበ ሻንጣ አለ

ጌታቸር፡ መነፅር፣ ቀለበት፣ ሃብል፣ ሰዓት፣ ጫማ አስወልቃችሁን አልነበረም?

ምስክር፡ አልነበረም

ጌታቸር፡  በባዶ እግር ወስዳችሁናል አልወሳዳችሁንም?

ምስክር፡ በባዶ እግር ነበራችሁ

ጌታቸር፡ የተሰበሰበውን ንብረት ምን አደረጋችሁት? ህዳር 10/2009 ከሸዋሮቢት ስንመጣ የተዘረፍነውን ንብረት መልሱልን ስሎት ፡ “ማረሚያቤቱን እንዳወደማችሁ የናንተንም ንብረት አውድመነዋል አላሉኝም?

ምስክር፡ አላልኩም

ጌታቸር፡ ነሃሴ 28/2008 ስንት ባስ ነው ወደ ሸዋሮቢት የሄደው?

ምስክር፡ አላስታውስም

ጌታቸር፡ እሺ እኔ ላስታውሶት 9 ባስ 870 ታራሚ ሄደናል፡፡ መቼም እርስዎ ዘጠኙም መኪና ውስጥ አይሆኑም፡፡ እንዲያውም በፒካፕ የሄዱ ይመስለኛል፡፡ ታዲያ የታራሚ ንብረት ሲወሰድ እየተከታተሉ ሲያዩ ነበር?

ምስክር፡ አላየሁም - አላውቅም

ዳኞች፡ አላየሁም እና አላውቅም ይለያያል፡፡ ንብረት እንደተወሰደ አላውቅም ነው ሲወሰድ አላየሁም?

ምስክር፡ የተወሰደ ንብረት የለም-አልተወሰደም

ጌታቸር፡ የተሰበሰበው ሻንጣ እና ንብረት አልደረሰንም፡፡ ታዲያ የት ደረሰ?

ምስክር፡ ተሰብስቦ ነበረ፡ ከቆይታ በኃላ ሲሸት እንዲወገድ ተደረጓል

ጌታቸር፡ ጠሃ እና ቴዎድሮስ የሚባሉት ታራሚዎች መረጃ ይሰጡኝ ነበር ብለዋል

ምስክር፡ አዎ

ጌታቸር፡ ቴዎድሮስ ያባቱ ስም ማነው?

ምስክር፡ አላቀውም

ጌታቸር፡ ቴድሮስ የሚባለው ከ23ቱ ሞቱ ከተባሉት ውስጥ አለ?

ምስክር፡ አዎ ስንተኛ ተራ ቁጥር ላይ እንደሆነ አላስታውሰውም

ጌታቸር፡ የተከበረው ፍርድ ቤት ከሱ የታይልኝ፡ ቴዎድሮስ የሚባል ሰው እንዳለ

ዳኞች፡ [ክሱን ላይ የተዘረዘሩትን 23ቱን ስም ዝርዝር ካዩ በኃላ] እኛ አይነተነዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ሲመረምር የሚታይ ነው የሚሆነው

- **በ15ኛ ተከሳሽ ፍቅረማርያም አስማማው እና በምስክሩ መካከል የነበረ ጥያቄና መልስ፡፡**

ፍቅረማርያም፡ የተከበረው ፍርድ ቤት ከራውን በነበረው ችሎት ምስክሩ አጅበውን ይመጡ ነበር፡፡ የሌሎች ምስክሮችን ቃል ሰምተዋል፡፡ እኛ የምስክር ዝርዝር ስላልደረሰን ምስክር እንደሆኑ አላወቅንም ነበር፡፡ ፍርድ ቤቱም ይህን ተከታትሎ አላስፈፀመልንም፡፡

ዳኞች፡ እንዲህ አይነት ጥቆማ ምስክሩ ከመጀመራቸው በፊት ቢሆን ጥሩ ነው፡፡ እኛ ያለፍነውን ነገር እናንተ ካያችሁ እየነገራችሁን ምንወስደውን እርምጃ እየወሰድን እንሄዳለን፡፡

ዳኞች፡ [ለምስክሩ] ከራውን በነበረው ችሎት አጅበዋቸው ይመጡ ነበር?

ምስክር፡ አዎ

ፍቅረማርያም፡ የተከሰሰነው በፀረ ሽብር አዋጁ እንደሆነ ያውቃል፡፡ እኛ በፊትም አዋጁን ስንቃወም የነበረው አንዱ በስሚ ስሚ ምስክር ዜጎችን እድሜ ልክ እና ሞት የሚያስፈርድ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ለምጠይቆት ጥያቄ ብቻ ቀጥተኛ ምላሽ እንዲሰጡኝ አሳስቦታለሁ፡፡

ፍቅረማርያም፡ አክሽፈነዋል ያሉት ከእስር ቤት የማምለጥ ዝግጅት ነበረ ብለዋል

ምስክር፡ አዎ

ፍቅረማርያም፡ እንዴት ነው ያከሸፉት? በጥይት የተመታ ሰው አለ?

ምስክር፡ የለም

ፍቅረማርያም፡ ወደ ሰማይ ተተኩሷል?

ምስክር፡ አልተተኮሰም

ፍቅረማርያም፡ ሊያመልጥ የነበረ እስረኛን በቁጣ ወይም በንግግር አስቁማችኃል?

ምስክር፡ አላስቆምንም

ፍቅረማርያም፡ ፖሊሶችን አፍነው ለመሄድ አቅደዋል ብለዋል፡፡ የታፈነ ፖሊስ ነበር እንዴ?

ምስክር፡ አልነበረም

ፍቅረማርያም፡ የሙከራ ዝግጅት ያሉት ነገር በተግባር የሚገለፅ ነገር ነበረው?

ምስክር፡ አልነበረውም

ፍቅረማርያም፡ ታዲያ አክሽፈነዋል ይባላል?

ምስክር፡ አዎ ሃሳቡን

ፍቅረማርያም፡ ያከሸፋችሁበት መንገድ?

ምስክር፡ የእለቱ ለት ወይም በዛ አካባቢ ስታስተባብሩ የነበራችሁትን ማግለያ ቤት ወስደናችኃል

ፍቅረማርያም፡ እኛን ማግለያ ቤት ስትወስዱ ለማምለጥ መሞከራችንን ከኛ አረጋግጣችኃል?

ምስክር፡ አላረጋገጥንም

ፍቅረማርያም፡ በማረሚያ ቤቱ አሰራር ያጠፋን ሰው ቃል ከመቀበል ጨምሮ ክስ እንደሚቀርብበት እና እንደሚቀጣ እናውቃለን፡፡ ከምሽቱ 4 ሰዓት ላይ ጮክ ብለህ አውርተህ ሰው ቀሰቅሰሃል ብሎ የሚቀጣ ማረሚያ ቤት ነው፡፡ ታዲያ እኛ ላይ እንዲህ አይነት ነገር ያልነበረው ለምንድነው? አዝናችሁልን ነው ወይስ የማምለጥ ሙከራ ስላልነበረ ነው?

ምስክር፡ ስላልነበረ ነው

ፍቅረማርያም፡ ለመፈታት አንድ ቀን የቀረው እስረኛ እንኳን ያመልጣል ተብሎ ስለሚጠበቅ በከፍተኛ ጥበቃ ነው አይደል የሚደረገው?

ዳኞች፡ ቆይ መጀመሪያ እስረኛ ያመልጣል ተብሎ ይታሰባል አይታሰብም የሚለውን ይመልሱ

ምስክር፡ እስረኛ ያመልጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡ አንድ ቀን ቢቀረውም ጥበቃው አይቀንስም

ፍቅረማርያም፡ እኛ በታሪክ ከእስር ቤት ያመለጡ ሰዎች እንደጀግና ሲታዩ ነው የምናየው፡፡ ኦፕሬሽን ኢጋዚ እና ዘመቻ ሙሴ ፊልሞችም ከእስር ቤት ያመለጡ ሰዎችን ያወድሳሉ፡፡ ከእስር ቤት ሊያመልጥ ያሰበ ሰው ወንጀለኛ ያስብለዋል?

ምስክር፡ ያስብለዋል፡፡ በህግ ይጠየቃል፡፡

ፍቅረማርያም፡ ትላንት ሲመሰክሩ ሊያመልጥ ያሰበን እስረኛ እግሩን እንመታዋለን እያለ እያለም እንገድለዋልን ብለዋል

ምስክር፡ እንገድለዋለን አላልኩም

ፍቅረማርያም፡ እሺ እግር እንመታለ ከዛ ቀጥሎ ደግሞ እናስቀራለን ብለዋል፡፡ የምታስቀሩት ከምን ያክል ርቀት ላይ ሲሆን ነው?

ምስክር፡ አላውቀውም

ፍቅረማርያም፡ የግቢው የመጨረሻ አጥር ግንብ ነው፡፡ ከዛ የሽቦ አጥር አለ፡፡ ከዛ የቆርቆሮ አለ፡፡ አንድ እስረኛ ሊያመልጥ ነው የሚባለው የት ቦታ ነው?

ምስክር፡ ከቤቱ ሲወጣ .. ከተፈቀደለት ግቢ ሲያልፍ

ፍቅረማርያም፡ 2ቱ በጥይት ሞቱ የተባሉት እስረኞች የቱ ጋር ነው የተገደሉት?

ምስክር፡ አላውቅም፡፡ በኢንፎርሜሽን ደረጃ መሞታቸውን ነው የሰማሁት፡፡

ፍቅረማርያም፡ እሺ ቆርቆሮው ስር ተገድሎ የሞተ ሰው አለ?

ምስክር፡ የለም

ፍቅረማርያም፡ የደረሰን ክስ ላይ ሁለቱ በጥይት ተመተው የሞቱት እስረኞች ፎቶ የሚታየው ቆርቆሮው ስር ነው፡፡ ቆርቆሮው ጋር ሰው ከሞተ ሊያመልጥ ሲል ነው ማለት ይቻላል?

ምስክር፡ አይቻልም

ፍቅረማርያም፡ በቃጠሎው ወቅት የት ነበርኩ?

ምስክር፡ ዝዋይ ይመስለኛል ..ተፈርዶቦት ነበር.. ከቃጠሎው የተወሰ ቀናት በፊት ወደ ዝዋይ ሄደዋል ይመስለኛል

ፍቅረማርያም፡ ላስታውሶት፡ ሃምሌ 29/2008 ተፈርዶብኝ ነሃሴ 14/2008 ወደ ዝዋይ ሄጃለው፡፡ ከዝዋይ ለምርመራ ያመጡኝ እርስዎ ኖት አይደል?

ምስክር፡ አዎ

ፍቅረማርያም፡ ኬት ነው ያመጡኝ? ተፈርዶባቸው ዝዋይ ከነበሩ ጋር ነው ወይስ ከቃጠሎ በኃላ ከቂሊንጦ ዝዋይ ከተወሰዱት ውስጥ?

ምስክር፡ ዝዋይ ተፈርዶባቸው ከነበሩት ውስጥ

ፍቅረማርያም፡ በቃጠሎ ወቅት የተሰበሰበው ብር ስንት ይሆናል?

ምስክር፡ አላስታውሰውም

ፍቅረማርያም፡ 100ሺ ይሆናል

ምስክር፡ ይሆናል

ፍቅረማርያም፡ 200ሺስ ይሆናል?

ምስክር፡ እኔንጃ

ፍቅረማርያም፡ ከማነው የተሰበሰበው?

ምስክር፡ ከተሰበሰበው ሻንጣ ነው የተሰበሰበው

ፍቅረማርያም፡ ግቢ ውስጥ 3ሺ የሚሆን እስረኛ አለ፡፡ ለአንድ ሰው 200 ብር እንደሚፈቀድ ተናግረዋል፡፡ ቢያንስ በቃጠሎው ወቅት ከእያንዳንዱ ታራሚ 100 ብር ቢገኝ 300ሺ ብር ታገኛላችሁ ማለት ነው፡፡ የተገኘው ብር የእከሌ ነው የምትሉት ነገር አግኝታችኃል?

ምስክር፡ ከሁሉም ነው ብሩ የተሰበሰበው፡፡ የማን የማን ነው አናውቅም፡፡

- **በ4ኛ ተከሳሽ አበበ ኡረርጌሳ እና በምስክሩ መካከል የነበረ ጥያቄና መልስ፡፡**

አበበ፡ ፌደራል ማረሚያ ቤት ውስጥ 20 ዓመት አገልግያለው ብለዋል፡፡ በማረሚያ ቤት ውስጥ ያለው የህግ የበላይነት ነው የሰው የበላይነት?

ምስክር፡ የህግ የበላይነት

አበበ፡ የህግ የበላይነት ካለ እነ ተስፋሁን ጨመዳ፣ ኒሞና ጥላሁን፣ አየለ በየነ፣ አብደታ ኦላንሳ እና የመሳሰሉት ህክምና ተከልክለው እንዲሁም ሌሎች በጥይት ሲገደሉ የተጠየቀ ሰው አለ?

ምስክር፡ በጥይት የሚገደል የለም

አበበ፡ ከዞን 2 ማግለያ ወደምትሉት ወደዞን 4 የወሰዱን እርስዎኖት አይደል?

ምስክር፡ አዎ

አበበ፡ እዛ ሲወስዱን ፤ እየወሰዱን ያለነው የአማራ እና ኦሮሞ ተወላጅ እንደሆንን እና ለምን ዘረኛ ይሆናሉ ብዬዎት አልነበረም?

ምስክር፡ ብለህ ሊሆን ይችላል፡፡ እኔ ግን በዘረኝነት አልሰራሁም

አበበ፡ ማረሚያ ቤቱ ከላይ እስከ ታች በአንድ ጎሳ የታጠረ ከመሆኑ የተነሳ እኛን የተገለልንበት ቦታ መጥታችሁ ስታናግሩን የነበራችሁት የአንድ ጎሳ አባላት አልነበራችሁም? ካነጋገራችሁን በኃላስ ሰድባችሁን አልሄዳችሁም?

ምስክር፡ እኔ ማንንም አልተሳደብኩም

አበበ፡ ከማረሚያ ቤት ለማምለጥ ስናቅድ ከሆነ የደረሳችሁብን ለምን ሳትከሱን አለፋችሁ?

ምስክር፡ በሃሳብ ደረጃ ብቻ ስለሆነ በማግለል ብቻ አለፍናችሁ

አበበ፡ እሺ፡ እኔ በወቅቱ "ምክንያቱን ሳላውቀው ቅጣት ቤት ገብቻለው" ብዬ ለፍርድ አመልክቼ እርሰዎ መልስ እንዲሰጡ ሲጠሩ " ለጥበቃ እንዲመቸን ነው" ብለው መልሰዋል አላሉም?

ምስክር፡ ብዬ ሊሆን ይችላል

አበበ፡ ለምን ተቀጥቼ እንደሆነ ለፍርድ ቤት አልተናገሩም?

ምስክር፡ በብዙ መዝገብ ላይ ምላሽ ስለምሰጥ እኔ ምን እንዳልኩ ትዝ አይለኝም፡፡

- **በ ኛ ተከሳሽ ዶ/ር ፍቅሩ ማሩ እና በምስክሩ መካከል የነበረ ጥያቄና መልስ፡፡**

ዶ/ር ፍቅሩ፡ በቃጠሎ ጊዜ የተሰበሰቡትን ንብረቶች አስወግደናል ብለዋል፡፡ የንብረት አወጋገድ ስርዓት አላችሁ?

ምስክር፡ አዎ

ዶ/ር ፍቅሩ፡ የማቃጠል መብት ማን ሰጣችሁ? የህግ አግባብ ይዛችሁ ነው? የአንድን ታራሚ ንብረት ወስዶ የማቃጠል ስልጣን ማረሚያ ቤቱ አለው?

ምስክር፡ የለውም

ዶ/ር ፍቅሩ፡ በእለቱ ጥይት ወዴት ነበር የሚተኮሰው?

ምስክር፡ ወደ የአቅጣጫው ይተኮስ ነበር

ዶ/ር ፍቅሩ፡ ወደ የአቅጣጫው ሲሉ?

ምስክር፡ ወደ ላይ

ዶ/ር ፍቅሩ፡ በሰዓቱ ከማረሚያ ቤቱ በውጪ በኩል እንደነበሩ ተናግረዋል፡፡ የሚተኮስበትን አቅጣጫ በምን አወቁ?

ምስክር፡ በግምት ነው

ዶ/ር ፍቅሩ፡ እንማን እንደሚተኩሱ እና ወዴት እንደሚተኩሱ ትእዛዝ ሰጥተዋል?

ምስክር፡ አልሰጠሁም

ዶ/ር ፍቅሩ፡ የማስተባበር ስራ ነበር የምሰራው ብለዋል፡፡ ማስተባበር ደግሞ የሚተኩሰውንም ይመለከታል፡፡ እሺ አቃቤ ህግ በማስረጃነት ባያያዘው የሰነድ ማስረጃ ገፅ 36 ላይ የእሳት እና አደጋ መከላከል ሪፖርት ያደረገው "በፀጥታ ክፍሉ ጥይት የመተኮስ እና የመናበብ ችግር" እንዳለ ይገልፃል፡፡ እሳት አደጋ እሳቱን ሊያጠፋ በመጣ ወቅት እናንተ ስትተኩሱ እንደነበር እና ስራቸውንም እንዳወካችሁ ነው የሚገልፀው፡፡

ምስክር፡ ስለሪፖርቱ የማውቀው ነገር የለም

ዶ/ር ፍቅሩ፡ አንድ ሰው ሲሸሽ ወደ ጥይት ወደሚተኮስበት ነው የሚሄደው ወይስ ወደ ማይተኮስበት?

ምስክር፡ ሸሺው ነው የሚያውቀው፡፡ ሸሺው በሚያዋጣው መንገድ

[በከሰዓቱ ችሎት ቶፊቅ የሚባል ተከሳሽ ምሳ ሰዓት ላይ ከቂሊንጦ የመጡ አባሪዎቹ ተፈቅዶላቸው ሲሰግዱ እሱ ግን እንዳይሰግድ ከቃሊቲ አጅቦት የመጣው ፖሊስ እንደከለከለው እና አመክሮህን ትበላለህ እያለ እንዳስፈራራው ገልፆ ስለተረበሸ እና ስላልሰገደ ወደ ቃሊቲ እንዲሄድ እንዲፈቀድለት ጠይቆ ነበር፡፡ ዳኛው ግን አጅቦት የመጣው ፖሊስ የግል ችግር ከሆነ በሌላ ጊዜ ሊሻሻልለት እንደሚችል በመጠቆም እሱ የሚሄድ ከሆነ ችሎቱም እንደሚቆም በመግለፃቸው ሌሎች ተከሳሾችም ቶፊቅን አግባብተውት ችሎቱ ቀጥሏል፡፡]

- **በ ጠበቃ ሙስጠፋ ሽፋ እና በምስክሩ መካከል የነበረ ጥያቄና መልስ፡፡**

ጠበቃ፡ ነሃሴ 28/2008 እርስዎ ሽጉጥ የዘው ነበር?

ምስክር፡ አዎ

ጠበቃ፡ ረብሻ ስለነበረ ነው ወይስ?

ምስክር፡ ረብሻ ባየኖርም እይዛለሁ

ጠበቃ፡ ነሃሴ 28/2008 ዶ/ር ፍቅሩ ነበሩ?

ምስክር፡ በነሃሴ 27/2008 ለህክምና ወደ ቃሊቲ ሄደዋል

ጠበቃ፡ ማን ፈቅዶ ነው የሄዱት

ምስክር፡ ሃኪም

ጠበቃ፡ አበበ ኡርጌሳ እና ሌሎች ወደ ማግለያ ቤት ተወስደዋል ብለዋል?

ምስክር፡ አዎ

ጠበቃ፡ እነሱ የነበሩበት ቦታ የተቃጠለበት ቦታ ነበር?

ምስክር፡ አልነበረም

ጠበቃ፡ አስከሬን ለፖሊስ ሰጠን ብላችኃል፡፡ ስንት አስከሬን ነበር?

ምስክር፡ 23

ጠበቃ፡ አስከሬን ማን ነው ያነሳው?

ምስክር፡ ፖሊስ

ጠበቃ፡ የደረሰውን ጉዳት ከቃጠሎው በኃላ ገብተው አየተዋል?

ምስክር፡ አላየሁም

ጠበቃ፡ ለምንድነው ገብተው ያላዩት?

ምስክር፡ ውጪ ስራ ስለነበረኝ ነው

ጠበቃ፡ ነሃሴ 28/2008 ወይም ከዛ በኃላ ግምገማ ስታደርጉ አባል ላይ አደጋ ደርሷል?

ምስክር፡ አዎ በድንጋይ የተመቱ አሉ ቁጥራቸው አላቀውም

ጠበቃ፡ ልክ የ23ቱን ታራሚዎች እንደተፃፈው የአባሎቹ ለምን አልተፃፈም?

ምስክር፡ 8 ይሆናሉ ጉዳት የደረሰባቸው አባላት

ጠበቃ፡ ስለምግቡ ጉዳይ የተወያያችሁት ከሁሉም ታራሚ ጋር ነበር?

ምስክር፡ አዎ

ጠበቃ፡ የታራሚው ምላሽ ምነበር?

ምስክር፡ የሚደግፍም የሚቃወምም አለ

ጠበቃ፡ አተት ተገኝቶ ነበር?

ምስክር፡ ዞን 3ት ውስጥ ተገኝቶ ነበር

- **በ18ኛ ተከሳሽ አንጋው ተገኘ እና በምስክሩ መካከል የነበረ ጥያቄና መልስ፡፡**

አንጋው፡ የተከበረው ፍርድ ቤት ምስክሩ ሽጉጥ ይዘው ከሆነ የፈተሹልኝ

ዳኞች፡ ሽጉጥ ይዘዋል

ምስክር፡ አልያዝኩም

አንጋው፡ ማረሚያ ቤቱ የእዝ ሰንሰለት አለው የለውም?

ምስክር፡ አለው

አንጋው፡ የቃጠሎው ቀን የእዝ ሰንሰለት ሳይጠበቅ ለምን ተተኮሰ?

ምስክር፡ ድንገተኛ ስለሆነ ሁሉም ኃላፊ እርምጃ ወስዷል

አንጋው፡ ከእስረኛ ጋር ፀብ የለኝም ይላሉ ነገር ግን እዚም ያለ እስረኛ የጮሃል ቃሊቲ ያለም ይጮሃል ለምንድነው?

ምስክር፡ አላውቅም

አንጋው፡ ከእስር ቤት የማምለጥ ሙከራው ላይ ነበርኩበት?

ምስክር፡ አዎ

አንጋው፡ ምን እርምጃ ወሰዳችሁብኝ? አገለላችሁኝ?

ምስክር፡ አላገለልንህም፡፡ ግን እየተከታተልንህ ነበር፡፡ አንዴ ሰማያዊ ነኝ ትላለህ አንዴ ግ7 ነኝ ትላለህ

አንጋው፡ የማምለጥ ዝግጅት ማለት?

ምስክር፡ ዞን 1 የማምለጥ ሙከራ የማነሳሳት ስራ ትሰራ ነበር

አንጋው፡ ማንን አስተባበርኩ?

ምስክር፡ ማን ማንን እንደሆነ አላውቅም፡፡ አባል ነው የነገረኝ፡፡

አንጋው፡ መንግስት የለም ብዬ አውርቼ ነበር?

ምስክር፡ አዎ፡፡ ኢንፎርሜሽን ደርሶኛል፡፡

አንጋው፡ በ29/12/2008 ሸዋሮቢት ጠዋት የቺን ጃኬት ለብሰው ካሳ መሃመድ ወይም ኩባን ምን እንደተናገሩት ያስታውሳሉ? ጥይት ነበር የሚገባህ አላሉትም?

ምስክር፡ አላልኩትም

አንጋው፡ ሸዋሮቢት ለማን ነው ያስረከቡን? የማነ ለሚባሉ ሃላፊ እና በ15/1/2009 አግባውን በሚስማር ለመታው አስገደ ተስፋዬ ጫካ ውስጥ አላስረከቡንም?

ምስክር፡ ጊቢ ውስጥ ነው ያስረከብኳችሁ

አንጋው፡ ስንት ጥይት ተኮሱ?

ምስክር፡ አልተኮስኩም

- **በድጋሚ ጥያቄ ተከሳሽ በአቃቤ ህግና እና በምስከሩ መካከል የነበረ ጥያቄና መልስ፡፡**

አቃቤ ህግ፡ በምን አግባብ ነው ዞን 1 እና ዞን 2 ይገናኙ የነበረው?

[ጥያቄውን ምስክሩ በግልፅ የመለሱት ስለሆነ መጠየቅ የለበትም በሚል ከተከሳሾች መቃወሚያ ገጥሞት የነበረ ቢሆንም አቃቤ ህግ ጥያቄውን እንዲቀጥል ዳኞች ወስነዋል፡፡]

ምስክር፡ ቀጥታ ግንኙነት የለም ግን ፌስታል በእንጀራ እየተጠቀለለ ወረቀት በውስጡ ተደርጎ ይላላካሉ

አቃቤ ህግ፡ ፍተሻ ካለ ብሩን እንዴት ነው የሚያስገቡት?

ምስክር፡ በህገ ወጥ ነው የሚገባው

አቃቤ ህግ፡ ዶ/ር ፍቅሩ ብሩ የገባላቸዋል የሚል መረጃ የደረሶት ለምን አገልግሎት ሊጠቀሙበት ነው?

ምስክር፡ ቃጠሎው እና ችግሩ እንዲነሳ

አቃቤ ህግ፡ መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ ለብቻቸው ለብቻ ጥበቃ ተደርጎላቸው ሲመላለሱ ነበር ብለዋል፡፡ መቼ ነው ለብቻቸው በጥበቃ ሲሄዱ የነበረው? ከቃጠሎው በፊት ነው በኃላ?

[ጥያቄው ከዚህ ቀደም የተመለሰ ስለሆነ መጠየቅ የለበትም በሚል ከመቶ አለቃ ማስረሻ መቃወሚያ ገጥሞት የነበረ ቢሆንም አቃቤ ህግ ጥያቄውን እንዲቀጥል ዳኞች ወስነዋል፡፡]

ምስክር፡ ከቃጠሎው በኃላ

አቃቤ ህግ፡ እነ መቶ አለቃ ማስረሻ ሰጤ እና ሌሎቹ ተገለው ከነበ እንዴት ሊያሰሳሱ የቻላሉ

ምስክር፡ በፍርድ ቤት ይገናኛሉ

አቃቤ ህግ፡ ብዙዎቹን የምስክርነት ቃልዎን ሲሰጡ ሰምቼ ነው ሲሉ ነበር፡፡ እንዴት ነው?

ምስክር፡ እለታዊ መረጃዎችን የሚሰበስቡት ሌሎች ናቸው፡፡ ከታራሚዎች ጋር ቀረቤታ ያላቸው፡፡ ከነሱ ነው መረጃውን የማገኘው፡፡

➤ **በፍርድ ቤቱ የማጣሪያ ጥያቄ የምስክሩ መልስ፡፡**

ዳኞች፡ ተኩስ ለመተኮስ እዝ ያስፈልጋል? ምን ሲሆን ነው ትእዛዝ የሚጠበቀው? ምን ሲሆን ነው ሃላፊ ራሱ እርምጃ የሚወስደው? በፅሁፍ የተቀመጠ ነገር አለ?

ምስክር፡ በፅሁፍ የተቀመጠ ነገር የለም፡፡ ዞሮ ዞሮ ችግር ከተነሳ አባል የራሱን እርምጃ ይወስዳል

ዳኞች፡ ገንዘብ እንደሚገባ መረጃ ይደርሰን ነበር ብለዋል፡፡ ለመያዝም እንቅስቃሴ አድርጋችሁ እንዳልተሳካላችሁ ተናግረዋል፡፡ የሚደርሳችሁ መረጃ ትክክለኛ መሆኑን በምን ማረጋገጥ ትችላላችሁ?

ምስክር፡ መረጃው እንደመጣ እንከታተላለን

ዳኞች፡ የቃጠሎ መነሻ የምግብ መከልከል ሆነ እንጂ እቅድ ስላላቸው ነው አመፅ ያነሳሱት ብለዋል፡፡ ምግብ ባይከለከል ኑሮ ቃጠሎ ወይም አመፅ ይነሳ ነበር?

ምስክር፡ የተወሰነ ቀን ጨምር ይሆናል እንጂ አይቀርም

ዳኞች፡ ስንት ቀን ይቆይ ነበር

ምስክር፡ አይታወቅም፡፡ መፈጠሩ ግን አይቀርም ነበር

ዳኞች፡ ገንዘቡ እንዴት ነው ለአመፁ መነሻ የሆነው?

ምስክር፡ በገንዘብ ሃይል የሚገዛ ሰው ስላለ እና ገንዘቡ ችግር ለሚፈጥሩ ሰዎች ስለተከፋፈለ

ዳኞች ፡ 15ኛ ተከሳሽ (ፍቅረማርያም አስማማው) ከቃጠሎው ከ15 ቀን በፊት ወደ ዝዋይ ሄዶ ነበር፡፡ ከዛም በፊት ማግለያ ቤት ነው የነበረው፡፡ ለምን ከዝዋይ እንዲመጣ አደረጉ? ምርመራ ውስጥ በምን መልኩ ተገናኝቶ ነው ያቀላቀላችሁት?

ምስክር፡ ምርመራ እየተካሄደ እያለ ነው እንዲጠራ የተደረገው፡፡ አምጡ ስለተባልን ነው ያመጣነው፡፡

ዳኞች፡ ሙቶ አለቃ ማስረሻ፣ ፍቅረማርያም እና አበበ ከቃጠሎው ከሁለት ወር በፊት ማግለያ ቤት ገብተዋል ብለዋል፡፡ ከቃጠሎው ጋር እንዴት ተገናኝተው ነው?

ምስክር፡ ማግለያ ከመግባታቸው በፊት ያነሳሱ ነበር፡፡ ከዛ በኃላም ፍርድ ቤት እና ሆስፒታል ይገናኛሉ፡፡

***የከሰዓቱ ችሎት ሰዐት አልቋል፡፡ ምስክሩም ምስክርነታቸውን በመጨረሳቸው እንዲመለሱ ተነግሯቸዋል፡፡ ቀሪ የኢቃቤ ህግ ምስክሮችን ለመስማት በተያዘው ቀጠሮ መሰረት ለነገ 26/4/2010 ተላልፏል፡፡***

# ታህሳስ 26/2020

➤ በቅድሚያ የሚመሰከረው አበበ ሻኒ የሚባል መሆኑን፣ በ30ኛ ተከሳሽ (አብዱልጋፋር) እና በ25ኛ ተከሳሽ (ደረጄ መርጋ) ላይ በ28/12/2008 በቂሊንጦ ቃጠሎ በህይወት እና በንብረት ላይ ለተፈጠረው አደጋ የነበራቸውን ተሳትፎ እና ከቃጠሎው በፊትም ዝግጅት እንደነበራቸው እንደሚያስረዱለት አቃቤ ህግ ተናግሯል።

➤ ምስክሩ እንዲቀርቡ በሚጠሩበት ጊዜ አለመኖራቸው ታውቋል። ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት እንዳላመጧቸው በማሳወቅ ሌላ ምስክር ቀድመው እንዲሰሙ እና የተጠቀሱት ምስክርን የቃሊቲ ማረሚያ ቤት ለከሰአት እንዲያቀርባቸው ዳኞች ትእዛዝ ሰጥተዋል። ተከሳሾቹ አቃቤ ህግ ከ5ወር በላይ ጊዜ ተሰጥቶት ምስክሮች አልመጡም አልቀረቡልኝም እያለ ጊዜ ሊፈጅባቸው እንደማይገባ፣ ከመካከላቸው ቀድሞ በቀረበባቸው ክስ ነፃ የተባሉ

እንዳሉ እና ለሚባክንባቸው ጊዜ ካሳ የሚያሰጥ የህግ አግባብ እንደሌለ ተናግረዋል። ምስክሮችን ለመጠበቅ የሚሰጠው ቀጠሮ እንዲታለፍ እና ብይን እንዲሰራላቸውም ጠይቀዋል።

- ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት የሚቀርበው ምስክር እስኪመጣ ሌላ ቀርቦ የነበረ ምስክር የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ አለማየሁ ብርሃኑ ይባላል ምስክሩ። በ9ኛ ተከሳሽ (ምትኩ ደበላ) ላይ እንደሚመሰክር ተናግሮ የሚከተለውን ምስክርነት ሰጥቷል፡፡

## ምስክሩ አቃቤ ህግ ባቀረበለት ዋና ጥያቄ መሰረት የሰጠው ምስክርነት

- ✓ ቃጠሎው በተከሰተበት ወቅት ታራሚ ሆነው ዞን አንድ እንደነበሩ እና በዞኑ የእስረኞች ኮሚቴ ሆነው ይሰሩ እንደነበር
- ✓ ነሃሴ 26/2008 ቀን የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር የቤተሰብ ምግብ አይገባም ብለው ከወሰኑ በኋላ የታራሚ ኮሚቴዎችን ሰብስበው እንደነገሯቸው ከዛም በየዞኑ እና በየቤቱ ለሚገኙ ሌሎች ታራሚዎች ንገሩ መባላቸውን
- ✓ የቤተሰብ ምግብ እንደማይገባ ለታራሚዎች ንገሩ ብለው ለሰበሰቧቸው አስተዳደር ሮች፤ በማረሚያ ቤቱ የበጀት እጥረት ስላለ ከቤተሰብ የሚመጣ ምግብ ከሌለ ማረሚያ ቤቱ የሚያቀርበው ምግብ በቂ እንዳልሆነ፣ ቢያንስ የበሰለ የቤተሰብ ምግብ እንዲገባ እንዲፈቀድ ካልሆነ ግን ከሌሎች ብሶቶች ጋር ተደማምረው ችግር ሊያስከትል ይችላል በማለት ሁሉም የታራሚዎች ተወካዮች ተቃውሟቸውን መግለፃቸውን
- ✓ የሰበሰቧቸው አስተዳደሮች ግን ያቀረቡትን ሃሳብ ሳይቀበሏቸው እንደቀሩ፣ የቤተሰብ ምግብ እንዳይገባ የተባለውም ዞን ሶስት ላይ አተት ተገኝቷል ተብሎ እንደሆነ
- ✓ ነሃሴ 27/2008 ማታ ላይ ጩኸት እንደነበረ፣ በነጋታው ጠዋት በራቸው ዘግይቶ መከፈቱን፣ ሊቆጥሯቸው የመጡ ፖሊሶችም የሚናገሩት ነገር ጥሩ እንዳልነበረ፣ ለቁርስ የመጣውን ዳቦ እየተነሳ መወርወር እንደተጀመረ፣ ሻዩም እንደፈሰሰ፣ ከቆጠራ በኋላ በየቤታቸው ገብተው በሩ እንደተዘጋባቸው፣ የተኩስ ድምፅም ይሰማ እንደነበረ፣ ትልቅ ድንጋይ ለአራት እና ለአምስት ይዘው ከተፈረካከሰ በኋላ ድንጋይ መወርወር እንደተጀመረ
- ✓ ተከሳሹ ምትኩ ደበላ ነሃሴ 28/2008 ቀን ጠዋት ላይ ይኖሩበት የነበረውን ቤት(5ኛ ቤት) በር ሲሰበር ተሳታፊ እንደነበር፣ በሩን ይሰብር የነበረውም የአልጋ ብረቶችን ተጠቅሞ እንደሆነ፣ የቤታቸውን በር በመስበር የታሰተፉት ሰዎች ወደ 12 እንደሚጠጉ፣ በተጨማሪም ተከሳሹ የማረሚያ ቤቱን ዩኒፎርም ማቃጠሉን እና ሌሎችንም ልብሳቸውን እንዲያወጡ እና እንዲያቃጥሉ ማድረጉን
- ✓ "ምትኩ ምን ስለሆነ ነው ሌሎቹን ልብስ አውጡ የሚለው?" ተብሎ ከአቃቤ ህግ ለቀረበለት የምስክሩ ምላሽ
- ✓ በአካል ሲታይ ገዘፍ ስለሚል እንጂ ሌሎችን ለመምራት እውቀትም የለውም የትምህርት ዝግጅት የለውም። ሌሎች ሲያደርጉ አይቶ ነው።" ሲል መልሷል።
- ✓ "አመፅ ለመምራት የትምህርት ዝግጅት ይጠይቃል?" ተብሎ ከአቃቤ ህግ ለቀረበለት ጥያቄ ምስክሩ "ግምቴ ነው" የሚል ምላሽ ሰጥቷል።

## ምስክሩ ከጠበቃ ሙስጠፋ ሽፋ  ለቀረበለት መስቀለኛ ጥያቄ የሰጠው ምስክርነት

ጠበቃ : የመሳሪያ ተኩስ ባይኖር ታራሚውን ማረጋጋት ይቻል ነበር?

ምስክር: ይቻላል

ጠበቃ: የቤተሰብ ምግብ አለመግባቱን በተመለከተ ለአስተዳደሩ ጋር የነበረው ስብሰባ መቼ ነበር? ስንት ነበራችሁ?

ምስክር: በ26/12/2008 ነበር ስብሰባው ከየዞኑ የተወከልን የታራሚ ኮሚቴዎች 20 እንሆን ነበር

ጠበቃ: 20ዎቻችሁም ተቃውሞ አቅርባችኋል?

ምስክር: አዎ

ጠበቃ: ለታራሚዎች ስትነግሩስ ተቃውሞ ገጥሟችኋል?

ምስክር: አዎ

ጠበቃ: በ28/12/2008 ተኩስ በነበረ ሰአት ሃላፊዎች ነበሩ?

ምስክር: ተከላይ አልነበረም። ገ/ማርያም ነበረ።

ጠበቃ: የሞተ ወይም የተጎዳ አይተሃል?

ምስክር: እኛ ዞን አላስታውስም

ጠበቃ: ነሃሴ 28/2008 ቆጠራ ተደርጓል?

ምስክር: አዎ

ጠበቃ: ሊቆጥሩ የነበሩ ፖሊሶች ሁኔታ ጥሩ አልነበረም ሲሉ?

ምስክር: ጥሩ ያልሆነ ነገር እያሳዩ እና እየተናገሩ ነበር የገቡት። የፖሊሶቹን ንግግር ስሰማ ፈርቼ ነበር።

ጠበቃ: ተኩሱ የነበረው ከቃጠሎው በፊት ነው

ምስክር: አዎ

ጠበቃ: ተኩሱ ወዴት ነበር?

ምስክር: ወደ ሰማይ

ጠበቃ: በምን አወቁ ወደ ሰማይ መሆኑን?

ምስክር: በግምት ነው

ጠበቃ: ምትኩ (ተከሳሽ) ዩኒፎርሙን አውልቆ የት ነው የጣለው?

ምስክር: ግቢ ውስጥ ዩኒፎርሞች እየተቃጠሉ የነበረበት ቦታ ነው። የሌሎችንም አቃጥሏል።

በጠበቃ ሰይድ አብደላ የቀረበ መስቀለኛ እና ምስክሩ የሰጠው መልስ

ጠበቃ: ምትኩ ሌሎች ሰዎችንም ዩኒፎርም አውጡ እያለ ያስገድድ ነበር ብለዋል አይደል?

ምስክር: አዎ

ጠበቃ: እሱ ራሱ በሌሎች ተገዶ ይሁን አይሁን የሚያውቁት ነገር አለ?

ምስክር: የለም

ጠበቃ: የምግብ መከልከሉ ጉዳይ ከሌሎች ብሶቶች ጋር ተጨምሮ ነው ሁኔታዎች የተባባሱት እና የቃጠሎ መንስኤ የሆነው ብለዋል። ሌሎች ብሶቶች ያሏቸው ምንድናቸው?

ምስክር: 1ኛ የምግቡ ጉዳይ ነው። ሁለተኛ የፍርድ መዘግየት ነው። ሶስተኛ ውስጣዊ ችግር ነው። ማረሚያ ቤቱ የሰጠው ዩኒፎርምም ተቃውሞ ነበረበት።

ጠበቃ: ምትኩ በሩን ሲመታ ነበር ሌሎችም አብረውት ነበሩ ብለዋል። ከብዙዎች መሃል እንዴት ለዩት? ምትኩ ምኑን ይምታ እንዴት ይምታ በምን ሊያውቁ ቻሉ?

ምስክር: ብዙ ሲባል በሺዎች የሚቆጠሩ ሳይሆን ከ5 እስከ 12 ይሆናሉ።

## ምስክሩ ከአቃቤ ህግ ለቀረበለት ድጋሜ ጥያቄ የሰጠው ምላሽ

አቃቤ ህግ: እርስዎ ልብስ አውልቀው ወርውረዋል?

ምስክር: ወርውሬአለሁ

አቃቤ ህግ: እናንተ ዞን ቃጠሎ ተነስቶ ነበር?

ምስክር: አልነበረም

አቃቤ ህግ: ዞን 2 እና ዞን 3 ቃጠሎ ነበር ብለዋል። ተኩሱ ከቃጠሎው በፊት መሆኑን በምን አወቁ?

ምስክር: መጀመሪያ ተኩስ ነበር ከዛ ነው ቃጠሎ የነበረው

አቃቤ ህግ: እናንተ ዞን ሆናችሁ የዞን 2 ወይም የዞን 3 መሬት ይታያችኋል እንዴ?

ምስክር: አይታየንም

አቃቤ ህግ: መሬት ላይ እሳት ቢኖር ይታያችኋል?

ምስክር: አይታየንም

አቃቤ ህግ: ምትኩ የተለያየ ተፅእኖዎች እንዳሉበት ተናግረዋል። በምን ሊያውቁ ቻሉ?

ምስክር: ከምትኩ ጋር አንድ አመት ኖረናል። በውስጡ ተፅእኖዎች እንዳሉበት አውቃለው።

አቃቤ ህግ: ቃጠሎው የተነሳው በምግብ ክልከላው እና ሌሎች ተፅእኖዎች ነው ብለዋል። ከነዚህ ተፅእኖዎቸወ ውጪ ሌሎች ምክንያቶች ይኑሩ አይኑሩ የሚያውቁት ነገር አለ?

ምስክር: የኔ እውቀት እዚ ድረስ ነው።

አቃቤ ህግ: ምትኩ ሌሎችን ሲያስፈራራ አይተዋል?

ምስክር: ሌሎችን በማየት ነው የተከተለው።

- ጠዋት ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት አልቀረበም ተብሎ የነበረው ምስክር በከሰአት ችሎት ቀርቦ ምስክርነቱን ሰጥቷል።
- የሚመሰከረው 30ኛ (አብዱልጋፋር) እና 25ኛ (ደረጀ መርጋ) ተከሳሾች ላይ እንደሆነ እንዲሁም በ28/12/2008 ቃጠሎው በተከሰተ እለት የተጠቀሱት ተከሳሾች የነበራቸውን ተሳትፎ እና ከዛም በፊት ዝግጅት ሲያደርጉ እንደነበር እንደሚያስረዳለት አቃቤ ህግ በጠዋቱ ችሎት መናገሩ የሚታወስ ነው

## ምስክሩ አበበ ሻኒ በአቃቤ ህግ ዋና ጥያቄ መሰረት የሰጠው ምስክርነት የሚከተለው ነው

- ✓ ተከሳሾቹን የሚያቃቸው ቂሊንጦ ዞን 3 ሁለተኛ ቤት አብረው ይኖሩበት በነበረበት ወቅት መሆኑን፤ ግንቦት ወር 2008 አካባቢ ዞን 3 ላይብረሪ ውስጥ በደረጀ እና አብዱልጋፋር መሪነት አመፅ ሊቀሰቅስ የሚችል ስብሰባ ማድረጋቸውን፤ በስብሰባው የተካፈሉት እስረኞች 60 እንደሚደርሱ እና ላይብረሪው ሞልቶ ውጪም ቆመው እንደነበር፤ እሱ (ምስክሩ) እና ሌሎች ጓደኞቹ ከላይብረሪው ፊት ለፊት ያለ ቦታ ላይ ባህላዊ የገበጣ ጨዋታ ይጫወቱ እንደነበር፤ በስብሰባው የሚያነሷቸው ነጥቦች በፍርድ ቤት ስለሚሰጧቸው ረጅም ቀጠሮዎች፣ ማረሚያ ቤቱ የሚያቀርበው ምግብ ጥራት ማነስ እና የምግብ በጀት እጥረት ጉዳይ መሆኑን፤ ተሰብስበው እያለም የዞን 3 ሃላፊ የሆነው በርሄ ሊያናግራቸው ሲመጣ የማረሚያ ቤት አስተዳደር ሃላፊውን ካልሆነ እሱን ማናገር እንደማይፈልጉ እንደገለፁለት፤ በስብሰባው የሚያነሷቸው ነጥቦች ለብጥብጥ እና ሁከት ለመፍጠር የሚጠቀሙባቸው ሰበቦች እንደሆኑ
- ✓ በ28/12/2008 ጠዋት ላይ ከቆጠራ በኋላ ሌላ ጊዜ ክፍት የሚሆነው የዞኑ በር እንደተዘጋ፤ ከዛም ከዞን 2 በጥቁር ፌስታል የተጠቀለለ ነገር እነሱ ወዳሉበት ዞን (ዞን 3) መወርወሩን፤ በፌስታሉ የተጠቀለለው ወረቀት ከተነበበ በኋላም ጭብጨባ እንደነበረ፤ በወረቀቱ የነበረው ነገር "እስከ 3 ሰአት በሩ ካልተከፈተ ብጥብጥ እናስነሳለን" የሚል ነገር መሆኑን
- ✓ ደረጀ መርጋ ዩኒፎርሙን ያላወጣ እናቱ ትበዳ እያለ ታራሚው ልብሱን እንዲጥል ሲያደርግ እንደነበረ

[ዳኞች በመሃል ገብተው "እርስዎ ትልቅ ሰው ስለሆኑ እንዲህ አይነት ቃል መጠቀም የለቦትም። ፀያፍ ቃል እያሉ መጠቀም ይችላሉ። ብለው አስተያየት ሰጥተውት ነበር። ምስክሩም "የነበረውን ሁኔታ እንደነበረ ለመግለፅ ነው" በማለት ምላሽ ሰጥቷል]

- ✓ በአብዱልጋፋር እና በደረጀ መሪነት እስረኛው ዩኒፎርም እያወጣ ግቢ ውስጥ ሲቃጠል እንደነበረ፤ በመቀጠል አብዱልጋፋር በእንጨት እሳቱን ከውጪ ይዞ ሁለተኛ ቤት ፍራሽ ላይ በማድረግ ቤቱ እንዲቃጣል ማድረጉን

- ✓ "ደረጀ መርጋ እኛን የጋምቤላ እና የቤንሻንጉል ልጆችን ከኛ ጋር መሰለፍ አለባችሁ። መሬታችሁ ለደቡብ ሱዳን ተሸጧል። ለዚህ ስርአት መገዛት የለባችሁም። እኛ የፖለቲካ እስረኞች ረጅም ቀጠሮ ነው የሚሰጠን።" እያለ ይቀሰቅሳቸው እንደነበረ
- ✓ "በተለይም የጋምቤላ እና የደቡብ ልጆች በትምህርት የገፉ ስላልሆኑ" በደረጀ መርጋ በኩል እነሱን የመጠቀም ነገር እንደነበረ
- ✓ የቤተሰብ ምግብ እንደማይገባ የሚገልፀው ማስታወቂያ የተለጠፈው በ27/12/2008 መሆኑን እና የተለጠፈውም ለታራሚው ጤንነት ሲባል መሆኑን
- ✓ አብዱልጋፋር ሁለተኛ ቤት ያለ ፍራሽ ላይ እሳት በመለኮሱ በዞኑ ያሉ 8 ቤቶች እና ሌሎች ንብረቶች መውደማቸውን እንዲሁም 4ኛ ቤት ሲቃጠል ውስጥ የነበረ ታደሰ ቦጋለ የሚባል አእምሮ በሽተኛ የሆነ እስረኛ መሞቱን

**ምስክሩ በተከሳሾች እና በጠበቆች የቀረቡለት መስቀለኛ ጥያቄዎች እና ምስክሩ የሰጣቸው መልሶች**

ጠበቃ [ኑሩ ሰይድ]: እርሶ ደረጀ በቀሰቀስዎ መሰረት በቃጠሎው ቀን ተሳትፈዋል?

ምስክር: አልተሳተፍኩም። ወደፊትም አልሳተፍም።

ጠበቃ [ኑሩ ሰይድ]: ከእርሶ ውጪ ደረጀ ሲቀሰቅሳቸው የነበሩ የቤኒሻንጉል እና የጋምቤላ ልጆች እነማን ናቸው?

ምስክር: ኤርሚያስ፣ ኢንስፔክተር ኢስሮም፣ ዳግም እና ሌሎችም በርካቶች

ጠበቃ [ኑሩ ሰይድ]: እነዚህ ልጆች በቃጠሎው ወቅት ተሳትፈዋል?

ምስክር: አልተሳተፉም

ጠበቃ [ኑሩ ሰይድ]: ላይብረሪ ተሰበሱ ያሉ ቀን ነው የዞን ተጠሪው በርሄ ያናገራቸው?

ምስክር: አዎ። ከዛ በኋላ ግን የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር እንዳወያያቸው መረጃው አለኝ

25ኛ ተከሳሽ ደረጀ መርጋ: እርስዎ በጉራፈረዳ የደህንነት እና የፀጥታ ዘርፍ ሃላፊ ነበሩ አይደል?

ምስክር: አዎ

25ኛ ተከሳሽ ደረጀ መርጋ: ስለ ደህንነት እና ፀጥታ ያውቃሉ ማለት ነው?

ምስክር: አዎ

25ኛ ተከሳሽ ደረጀ መርጋ: እኛ ለአመፅ እና ሁከት ስናደራጅ የሚያውቁ ከሆነ ለምን ለሃላፊ አልተናገሩም ወይም አላመለከቱም?

ምስክር: ለዞን ሶስት ተጠሪዎች አመልክቻለው

25ኛ ተከሳሽ ደረጀ መርጋ: እርስዎ በግል ፀባይዎ ለአማራና ለኦሮሞ ጥላቻ አሎት አይደል? ምክንያቱም በፌደራል ደረጃ ታዝዤ በጉራፈረዳ ኦሮሞና አማራን ጨርሼ ነው የመጣሁት ብለውናል አይደል?

[ጥያቄው በአቃቤ ህግ ተቃውሞ ቀርቦበታል። ምስክሩ ስለብሄር የመሰከሩትም ነገር የለም ከጭብጡ ጋርም አይገናኝም በሚል። ዳኞችም በአብላጫ ድምፅ ጥያቄውን ቀይሮ አስተካክሎ ይጠይቅ ብለው ወስነዋል። የልዩነቱ ሃሳብ "ምስክሩ ሲመሰክሩ ብሄር ተኮር የሆነ ምስክርነት ሰጥተዋል። ስለዚህ ፀብ ይኑረው አይኑረው ለማወቅ በተከሳሹ የቀረበው ጥያቄ መቅረብ ነበረበት" የሚል ነው።]

25ኛ ተከሳሽ ደረጀ መርጋ: እሺ ጥያቄዬን አስተካክላለሁ። በግልህ ይሄ መንግስት አሸባሪ እያለ የሚከሳቸውን ትጠላለህ አይደል?

ምስክር: ሰው ሰው ሆኖ በመፈጠሩ ማንንም አልጠላም

ዳኛ: ምስክር ጥያቄውን በስትክክል እያዳምጡ። ጥያቄው ሰው ትጠላለህ ሳይሆን በሽብር የሚከሰሱትን ትጠላለህ ወይ ነው

ምስክር: አልጠላም

25ኛ ተከሳሽ ደረጀ መርጋ: ላይብረሪ ውስጥ ስብሰባ ሲያደርጉ ነበር ብለዋል። ሃላፊ መጥቶ ያናግረን ሲሉም ነበር ብለዋል። ሁከት እና ብጥብጥ ለመፍጠር ማሰብ እና ሃላፊ ያናግረን ማለት አንድ ናቸው?

ምስክር: አመፅ ለማነሳሳት እና ደም ለማፋሰስ ነው አላማችሁ

25ኛ ተከሳሽ ደረጀ መርጋ: ስለ ምግብ ጥራት ችግር አለ ብሎ የሚያምን ሰው ሃላፊ ቢያናግር ችግር አለው?

ምስክር: ችግር የለውም። እናንተ ግን የዞን ተጠሪን ሳታናግሩ የአስተዳደር ሃላፊ ያናግረን አላችሁ።

25ኛ ተከሳሽ ደረጀ መርጋ: ቃሊቲ ያሉት ተፈርዶቦት ነው አይደል?

ምስክር: በጊዜ ቀጠሮ ነው ያለሁት። ቃሊቲ ያለሁት በጤና መታወክ ኬዝ ነው።

25ኛ ተከሳሽ ደረጀ መርጋ: ተፈርዶቦት ነው አይደል?

ምስክር: ቀጠሮ ላይ ነኝ።

ዳኛ: ቀጠሮ ማለት ምን ደረጃ ላይ ነው?

ምስክር: ጥፋተኛ ተብያለሁ

25ኛ ተከሳሽ ደረጀ መርጋ: የእርስ በርስ ግጭት በማነሳሳት ነው አይደል ጥፋተኛ የተባሉት?

[ጥያቄው ከአቃቤ ህግ ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የለውም በሚል ውድቅ እንዲሆን መቃወሚያ ቀርቦበታል። ዳኞችም በአብላጫ ድምፅ ጥያቄው ውድቅ እንዲሆን ውሳኔ ሰጥተዋል። የልዩነት ሃሳቡ "ምስክሩ ያለበትን ሁኔታ እንዲናገር ተደርጓል። ጥፋተኛ የተባለው በምን ጉዳይ መሆኑ ከመዝገቡ ይረዳል። ሊጠየቅ ይገባ ነበር።" የሚል ነው።]

ጠበቃ: ጥፋተኛ የተባሉበት መዝገብ የሚታየው የትኛው ችሎት ነው? የመዝገብ ስሙና ቁጥሩስ?

ምስክር: 19ኛ ችሎት (ምስክሩ እየመሰከሩበት ያለው ችሎት) ፣ በእነ ፃዲቄ ፍራ መዝገብ፣ ቁጥሩ ...

ጠበቃ: ላይብረሪው አካባቢ 60 ሰዎች አካባቢ ተሰብስበው ነበር ብለዋል። ማረሚያ ቤት ላይብረሪ ውስጥ ስብሰባ ማካሄድ ይፈቀዳል እንዴ?

ምስክር: አይፈቀድም

ጠበቃ: በመሰብሰባቸው ምክንያት ማረሚያ ቤቱ የወሰደው እርምጃ አለ?

ምስክር: ተገልለዋል

ጠበቃ: የማረሚያ ቤቱ ሃላፊ ያናግረን፣ የዞን ተጠሪ አያናግረን ብለዋል። ያነሷቸው የነበሩ ጥያቄዎች በዞን ተጠሪ የሚመለሱ ናቸው?

ምስክር: እንደ አሰራር ለዞን ተጠሪ ተነግሮ ነው ለተቋሙ ሃላፊ የሚነገረው

30ኛ ተከሳሽ አብዱልጋፋር: እኔና አንተ እንት እንተዋወቃለን አይደል?

ምስክር: አዎ። አንድ ቤተክርስቲያን ነው የምናመልከው። ኖርማል በሆነ መንገድ እንገናኛለን።

30ኛ ተከሳሽ አብዱልጋፋር: አይተሸኛል እኔ ሙስሊም ነኝ።

[ምስክሩ ቀና ብሎ ካየው በኋላ ሊመሰክርበት ከመጣው ከሌላኛው ተከሳሽ ጋር እንደተምታታበት ገልፆል]

30ኛ ተከሳሽ አብዱልጋፋር: ስለ ታሰርንበት ኬዝም እናወራለን?

ምስክር: አዎ

30ኛ ተከሳሽ አብዱልጋፋር: አንተ የገባህበት በዘር ጭፍጨፋ መሆኑን ነግረኸኝ፣ ቀላ ያሉትን ሃበሾችን ማጥፋት እንፈልጋለን አላልከኝም?

ምስክር: አላልኩህም ወደፊትም ቢሆን አልልህም

30ኛ ተከሳሽ አብዱልጋፋር: ወታደር ነበርክ አይደል?

ምስክር: አዎ። የሃገር መከላከያ ሰራዊት
በድጋሜ ጥያቄ ምስክሩ ለአቃቤ ህግ የሰጠው ምላሽ
አቃቤ ህግ: እነ ደረጄ ሲሰበሱ በነበረ ወቅት ያነሱት የነበረውን ሃሳብ መጠቀሚያ አድርገው ሁከት ለማስነሳት ፈልገው ው ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው ነው?
ምስክር: ጥራት የለውም የሚሉት ምግብ ሁለት አመት ስንበላው የነበረው ምግብ ነው። ምንም አዲስ ነገር የተከሰተ አልነበረም። ተቃጥሎ ለሞተው ልጅም ምክንያት ደረጄ እና አብዱልጋፋር ናቸው።
የዳኞ ማጣሪያ ጥያቄ
ዳኛ: እርስዎ የሞት ምክንያት ማወቅ ይችላሉ?
ምስክር: በመሰረቱ በእሳት ነው የተቃጠለው። ለእሳቱ መነሳት ደግሞ መንስኤ ደረጀ እና አብዱልጋፋር ናቸው። ልጁ ቤት ውስጥ ከነበረ ተቃጥሏል ማለት ነው።
ዳኛ: ሲሞት አይተዋል
ምስክር: አይቻለው
ዳኛ: እስቲ እንዴት ነው ያዩት
ምስክር: ቤቱ ሙሉ ለሙሉ ሲቃጠል አይቻለው። ሰዎች ጎትተው ሊያወጡት ሲሉ አእምሮውን ያመው ስለነበረ አልወጣም ብሎ ወደ ቤቱ ገብቷል። ቤቱ ተቃጠለ ማለት እሱም ተቃጠለ ማለት ነው

ዳኛ: በእሳት ተቃጥሎ ሲሞት አይተዋል
ምስክር: በአይኔ አላየሁም። በሪፖርት ሲነገር ነው የሰማሁት።
ዳኛ: ከዞን ሁለት ተወረወረ ያሉት ወረቀት ይዘቱ ምን አይነት ስሜት ነው ሚሰጠው?
ምስክር: በዞናችን ሁከት እና ብጥብጥ ለማስነሳት የተዘጋጁ ሰዎች ሲያገኙት አጨበጨቡ " ሁከት እና ብጥብጥ እንጀምራለን" የሚል ነው መልእክቱ

- ምስክሩ ምስክርነቱት በመጨረሱ እንዲ መለስ ተደርጓል
- ቀሪ የአቃቤ ህግ ምስክሮችን ለመስማትም ለነገ ታህሳስ 27/2010 የተያዘው ቀጠሮ እንደተጠበቀ መሆኑ ተነግሯል።

# ታህሳስ 27/2010

- አቃቤ ህግ ምስክር እንዳላመጣ፤ ቀጣይ ቀናት ምስክር ለማሰማት አስቀድሞ የተያዙ በመሆናቸው በቀጠይ ቀጠሮዎች ምስክሮቹን አቅርቦ እንዲያሰማ ጥያቄ አቅርቧል።

- ተከሳሾች እና ጠበቆች አቃቤ ህግ በተሰጠው ጊዜ ተጠቅሞ ምስክር ማቅረብ እንደነበረበት በመጥቀስ ተጨማሪ ቀጠሮ እንዳይሰጠው ጠይቀዋል።

- ዳኞችም እስከ ጥር 3 የተያዘው ቀጠሮ የአቃቤ ህግ ምስክሮችን ለመስማት በመሆኑ፤ የተያዘው ቀጠሮ ሳይደርስ ውሳኔ መስጠት እንደማይችሉ በመግለፅ አቃቤ ህግ በተያዘለት ቀጠሮ አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ ምስክሮቹን እንዲያቀርብ አሳስበዋል።

# ታህሳስ 30/2010

- አቃቤ ህግ ምስክሮች እንዳልቀረቡለት እና ፖሊስ ምስክሮቹን ማግኘት እንዳልቻለ ግን ጥረት እያደረገ በመሆኑ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጠው በመጠየቁ ምንም ምስክር ሳይሰማ ተከሳሾቹ እንዲመለሱ ተደርጓል።

- ዶ/ር ፍቅሩ ማሩ "ማርም ሲበዛ ይመራል። እዚህ ስመጣ በካቴና ታስሬ አደጋ ቢደርስ መውጣት በማልችልበት በሽቦ በታጠረ መኪና ነው የምመጣው። ከብት እንኳን ማእረግ አለው። አቃቤ ህግ ህሊና የላቸውም። አንዴ ተቀጥሮልኛልና እየታሰሩ ይምጡልኝ ነው የሚሉት። ምስክሮቻቸው የማይመጡ ከሆነ ይንገሩንና እዛው እንቀመጥ። በቃ መረረኝ 4ዓመት ከ8 ወር መረረኝ። የኔ በሽተኞች የሞቱት 20 ደርሰዋል። ቤተሰብ የሚፈቀድልን ከጠዋት 3 ሰአተ እስከ 6 ነው። እኛም እዚህ እየዋልን ቤተሰቦቻችንም እየዋሉ ነው። መቀየሪያ ልብስ እንኳን የለንም። በዚች ልብስ ነው ምንመላለሰው።"

- ዳኞች አቃቤ ህግ የሚሰጠውን ምላሽ እየመዘገቡ መሆኑን፤ ፍርድ ቤት ያዘዘው ፖሊስን ሆኖ እያለ ፖሊስ ለፍርድ ቤት ምንም ምላሽ እየሰጠ አለመሆኑን የተገነዘቡ መሆኑን፤ የተያዘውን ቀጠሮ ከመጠቀ ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለ ነገር ግን በመጨረሻው ቀን በጉዳዩ ላይ ብይን እንደሚሰጥበት ተናግረዋል።

# ጥር 1/2010

- ዛሬም ምስክር አልቀረበም። አቃቤ ህግ " ከፖሊሶች ጋር እየተነጋገርን ነው። ምስክሮች ጋርም በስልክ እየደወልን ነው። ጥረት እያደረግን ነው። በቃጣይ ቀጠሮ ፖሊስ እንዲያቀርብ እንዲታዘዝልን።" በማለት ጥያቄ አቅርቧል።

- ዳኞች "በእያንዳንዱ ቀጠሮ ፖሊስ ምስክሮችን ያላቀረበበትን ምክንያት እንዲያቀርብ ታዞ ነበር። ዛሬም እስከዛሬ ያላቀረበቡበትን ምክንያት እንዲሁም ዛሬም ያላቀረቡበትን ምክንያት አልገለፀም። ይህ እና አቃቤ ህግ ምስክሩን በተሰጠው ቀጠሮ አለማቅረቡ የሚጎዳው እሱን ነው። ጠበቆችም እየተጉላላችሁ እንደሆነ ይገባናል። ተከሳሾችም እንዲሁ። "

- 31ኛ ተከሳሽ ጌታቸር " አቃቤህጎች ቀን በቀን የተለያየ ሃሳብ ይዘው ይመጣሉ። አቃቤ ህግ ቀን በቀን ይቀያየራል። ከመስከረም 20/2009 እስከ ጥቅምት 14/2009 ባለው ጊዜ የ159 ታራሚ ምርመራ ጨርሰው ነው የተመለሱት። አሁን ከ5ት ወር በኋላ ስንመለስ አምስት ምስክር ነው ሊያሰሙ የቻሉት። አቃቤ ህግ የፈለገው ረጅም ቀጠሮ ሰጥቶ ጊዜውን ማራዘም እና እኛን ማጉላላት ነው።"

# ጥር 2/2010

- አቃቤ ህግ፡- "የቀረበ ምስክር የለኝም"
- ተከሳሾች እና ጠበቆች፡- "ከስከዛሬው የተለየ ሃሳብ የለንም"
- ዳኞች፡- "ነገ የአቃቤ ህግን ምስክር ለመስማት የተያዘው ቀጠሮ የመጨረሻው ቀን ነው። ነገ የሚመጣ ካለ እናያለን። ካልመጣ ትእዛዝ እንሰጣልን።

# ጥር 3/2010

- አቃቤ ህግ፡- "ዛሬ የቀረበ ምስክር የለኝም። ሁለት ምስክሮቼ መጥሪያ ደርሷቸው ያልቀረቡ ናቸው ታስረው በተለዋጭ ቀጠሮ እንዲቀርቡ ይታዘዝልኝ። አንድ ምስክሬ መቀሌ ነው የሚገኘው ስለታመመ ሊቀርብልኝ አልቻለም። ባጠቃላይ 28 ምስክሮች ይቀሩኛል። የተቀሩት ምስክሮች ያስመዘገቡት የሚገኙበትን ማረሚያ ቤት ስለነበረ በሚፈቱበት ወቅት የሚኖሩበት አድራሻ ማግኘት አስቸጋሪ ስለሆነ ነው ፖሊስ ሊያገኛ ቸው ያልቻለው። ስለዚህ ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጠን እና አፈላልገን እናቀርባለን።"

- አቃቤ ህግ በቂ ጊዜ ተሰጥቶት እንደነበረ እና በተሰጠው ረጅም ጊዜ ምስክሮቹን ማቅረብ ይችል እንደነበረ እንዲሁም ታመውብኛል ያላቸው አንድ ምስክር መታመማቸውን የሚገልፅ ማስረጃ ባለማቅረቡ፤ ምስክር የማሰማት መብቱ ታልፎ በተሰሙ ምስክሮች ብይን እንዲሰራ ተከሳሾች እና ጠበቆቻቸው ጠይቀዋል።

- ተከሳሾች አቃቤ ህጉን በመውቀስ በብስጭት የተለያየ አስተያየት ሰጠተዋል፡፡

- ዳኞች በአቃቤ ህግ እና ተከሳሾች የተደረገውን ክርክር መርምረው በነገው እለት (በ4/5/2010) ብይን እንደሚሰጡ ገልፀዋል።

# ጥር 4/2010

- 18ኛ ተከሳሽ [አንጋው ተገኘ] "አሞኛል አልወጣም" ብሎ ሲጠራ ሳይወጣ በመቅረቱ ወደ ፍርድ ቤት እንዳልመጣ ሊታወቅ ችሏል።

- የ18ኛ ተከሳሽ መቅረት የብይኑን መነበብ ስለማያግደው በሚል ብይኑ ለተቀሩት ተከሳሾች ተነበላቸዋል።

- አቃቤ ህግ ከግንቦት 14 እስከ 24/2009 ፣ ከነሃሴ 1 እስከ 12/ 2009 እንዲሁም ከታህሳስ 23 እስከ ጥር 3/2010 ረጃጅም ቀጠሮ እየተሰጠው ምስክሮቹን እንዲያሰማ ተለዋጭ ቀጠሮ እየተሰጠው እንደነበር እንዲሁም ፤ በመጨረሻ በነበረው ቀጠሮም (ከታህሳስ 23 እስከ ጥር 3/2010) አቃቤ ህግ ከተሰጠው 9 ቀን 4ቱን ቀን ብቻ በመጠቀሙ ፍርድ ቤቱ ስራ ፈቶ አምስት ቀን የአቃቤ ህግ ምስክሮች ይቀርባሉ ብሎ ሲጠብቅ እንደነበረ ዳኞች ተናግረዋል።

- ኢትዮጵያ በፈረመችው የአለም አቀፍ ሰብአዊ መብት ድንጋጌ አንቀፅ 14(3) ላይ አንድ ተከሳሽ አግባብ ባልሆነ ሁኔታ ሳይዘገይ የመዳኘት መብት እንዳለው እንደሚደነግግ እና ኢትዮጵያም ይህ ድንጋጌ የህገመንግስቱ አካል ማድረጓን ፤ ስለሆነም የወንጀል ህጉ አንቀፅ 94 (ለ) ላይ ተለዋጭ ቀጠሮ የሚጠየቅበት አግባብ ገደብ እንዳለው ዳኞቹ የገለፁ ሲሆን

  *1ኛ ፈርመው የቀሩት ሁለት ምስክሮች በአቃቤ ህግም በፖሊስም ስህተት ባለመሆኑ በቀጣይ ቀጠሮ ለ24 ሰአት ታስረው እንዲቀርቡ*

  *2ኛ ታመው ነው የቀሩት የተባሉት አንድ ምስክር የታመሙ ስለመሆናቸው ማስረጃ ባለመቅረቡ እንዲታለፉ 3ኛ ቀሪ አድራሻቸው ያልተገኙ ምስክሮች ኢቃቤ ህግ ሰፊ ጊዜ ተሰጥቶት እያለ ሳያቀርባቸው የቀሩ በመሆኑ እና አድራሻቸው የማይታወቅ በመሆኑ የተከሳሾቹን የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት ህገመንግስታዊ መብት ስለሚጋፋ እንዲታለፉ*

  *4ኛ ታስረው እንዲቀርቡ የተባሉትን የኢቃቤ ህግ ምስክሮች ለመስማት በማለት ቀጠሮ ለጥር 18/2010 ሰጥተዋል።*